ልሳነ ኢኮኖሚክስ

# ECONOMIC FOCUS

Bulletin of the Ethiopian Economic Association (EEA)

VOL. 6 NO. 2
November 2003

# ርዕይ 2020 በኢትዮጵያ

## በዚህ እትም

- ✓ ከአዘጋጁ
- ✓ ርዕይ፤ ኢትዮ□ያ በ2020 ከየት ወዴት? መስፍን ወልደ ማርያም
- ✓ Vision 2020: Whither Ethiopia / Mesfin Woldemariam

  Translated by Yonas Admassu

**በፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም ጽሁፍ ላይ የተሰጡ አስተያየቶች**

- ✓ / ደሳለኝ ራህመቶ
- ✓ / አሰፋ በቀለ

**ሌሎች**

- ✓ / ከአገር ውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በአገር እድገት የሚኖራቸው ሚና/ ብርሃኑ ነጋ

EDITOR-IN-CHIEF

Assefa Admassie

GUEST EDITOR

Mulat Demeke

EDITORIAL BOARD

Alemayehu Seyoum
Alemu Mekonnen
Eyob Tesfaye
Getnet Alemu
Gezahegn Ayele
Ishak Diwan

Web Postmaster

Metasebia Zelalem

© Ethiopian Economic Association (EEA)

All rights reserved.
No part of this publication can be reproduced, stored in a retrieval system or transmitted in any form without a written permission from the Ethiopian Economic Association.

| P. O. BOX | TELEPHONE | FAX | ADDIS ABABA |
|---|---|---|---|
| 34282 | 557459/113670 | 565252 | ETHIOPIA |

E-mail Address: eea@telecom.net.et Website: www.eeaecon.org

# ከአዘጋጁ

የሀገራችን የወደፊት ዕጣ ፈንታ ማነጋገር ከጀመረ ትንሽ ሰንበት ማለቱ ይታወሳል:: ችግሮቻችን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየሰፉና ሥር እየሰደዱ በመሆናቸው የት ልንደርስ ነው የሚል ጥያቄ በአንዳንድ አካባቢ መነሳቱ አልቀረም:: በሌላው አገር ችግር ብልሃትን እየወለደ በዕድገት ጎዳና መራመድ መቻሉን ብናይም፣ በሀገራችን ግን ችግር ችግርን እየወለደ ዕድገታችን ወደኋላ ከሆነ ከ30 ዓመት በላይ አስቆጥረናል:: በመሆኑም አብዛኛው ሕዝብ ከዕለት ጉርሱ በላይ ለማሰብ አቅም ያጣበት ደረጃ ላይ ደርሰናል::

አሁን ሀገራችን ያለችበት አሳዛኝ ሁኔታ መቀየር ካለበት የግድ በፕሮፌሰር መስፍን አባባል "የዕውቀት ባለሀብት" የሆነው ክፍል የረጅም ጊዜ ርዕይ ይዞ በመነሳት ሕዝብ ከድህነት የሚላቀቅበትን መንገድ መቀየስ አለበት:: የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር "ርክ□ 2020 በኢትዮጵያ" ብሎ ሲነሳ ዓላማው የዕድገት መሥመራችን ትክክለኛ አቅጣጫ ይዞ በመሄድ የሚቀጥለው ትውልድ የተሻለ ህይወት የሚኖርበትን ዕድል ለመፍጠር የበኩሉን አስተዋፅኦ ለማድረግ ነው::

የዛሬው ጽሑፍ አቅራቢ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም በሀገራችን ካሉ ምሁራን ሁሉ የበለጠ □ታወቃሉ:: ይህም ያለ ምክንያት አይደለም ስለአገራችን ልማትና ዕድገት ከማንም የተሻለ ብዙ ጽፈዋል:: ከማንም የበለጠ ለረጅም ዘመን በችግሮቻችን ዙሪያ በጥልቀት፣ በነፃ፣ በማሰብና መሆን የሚገባውን በድፍረት ያለምንም አድርባይነት ለማስረዳት ጥረዋል:: ከፍተኛ መስ□ዕትነትንም በ□□□□ ለመ□□ል ተ□□□ል::

□ሮ□ሰር መስፍን በዚህ ጹሑፋቸው እንደተለመደው ከዳበረው የዕውቀት ሀብታቸው በርካታ ቁምነገሮችን ቀንጨብ አድርገው እንደ አቶ ደሳለኝ ራህመቶ አባባል "መ□ሐ□ ቅዐ ሳዊ" የሚመስሉትን ወይም በዶ/ር አሰፋ በቀለ አባባል "ሊታለፍ የማይችል አስፈሪና አስደንጋጭ" ርዕያቸውን በአጭሩ አቅርበዋል:: ለዚህም ትብብራቸው በማህበሩ ስም ከፍተኛ ምስጋና አቀርባለሁ:: በእሳቸው ሃሳብ ላይ አስተያየታቸውን ለሰጡን ለአቶ ደሳለኝ ራህመቶና ለዶ/ር አሰፋ በቀለም ምስጋና አቀርባለሁ::

**THIS BULLETIN AND OTHER PUBLICATIONS OF EEA ARE SPONSORED BY FREIDRICH EBERT STIFTUNG OF GERMANY (FES), EMBASSIES OF UK, SWEDEN, NORWAY, NETHERLANDS AND THE AFRICAN CAPACITY BUILDING FOUNDATION (ACBF)**

# ርዕይ
# ኢትዮጵያ በ2020 - ከየት ወዴት?

መስፍን ወልደ ማርያም

## 1. መፅቢጸ

ያለንበትን ዓለም አጠቃላይ ሁኔ□ መገንዘብ □ሚጸስ□ልፅ □መስለኛል፤ መስከረም 1 ቀን 1993 በአሜሪካ ላይ የደረሰው አስከፊና አረመኔያዊ ጥቃት፣ አሜሪካ ለዚያ መልስ በአፍጋኒስታን፣ ቀጥሎም በኢራቅ የወሰደችው ተመሳሳይ ወ□□ራዊ እርምጃ፣ በሰሜን ኮሬአ፣ በሶርያና በ□ርስ ላ□ □ም□ሰማው ዛቻ፣ □እስልምና አክራሪዎች በሚባሉት በኩልም በኬንያ፣ በኢንዶኒዢያ፣ በኢራቅና በአፍጋኒስታን የሚደረገው ሁሉ በቋፍ ያለውን የዓለም ሰላም □□ደፈረሰ ነው:: ምናልባትም ለ□ህ ሁሉ ፌሱ □ □ ል ስ ዓ ኤ ማ □ ጸ ን ና □እስራኤላውያን መጨረሻው □ማ□□□፣ ክፋትና ጭካኔ የተሞላበት ግብግብ ሳይሆን አይቀርም:: በአንድ በኩል በማይመጣጠን □□ል □ሚ□ቀም ጭቆና ፍልስጥኤማዊነትን ወደ አረብነት፣ ከዚያም ወደ እስላምነት ሲለውጥ፣ በሌላ በኩል ደግሞ እስራኤላዊነትን ወደ ምዕራባዊነት ወይም ወደ አሜሪካንነት □□ለ□□ ነው:: ሰለዚህም የግብግቡ ኢላማ በጣም የሰፋና የተለያየ ሲሆን፣ □ፅብፅቡም መሣሪጸ በ□ም የተለያየ ሆኖአል:: በ□ልስዓ ኤማውያኑና በደጋፊዎቻቸው በኩል ኢላማው የአሜሪካን ወገን የሆነ ሁሉ፣ የአሜሪካ ንብረት የሆነ ሁሉ፣ ለአሜሪካ ጥቅም የዋለ ነገር ሁሉ ነው:: በአሜሪካና በእስራኤል በኩል ኢላማው ሽብርተኛ የሚሉት ነው:: ለቀሪው የዓለም ሕዝብ በሁለቱም ወገን የሚሰጠው ምርጫ የኔ ወገን ካልሆንህ የጠላት ወገን ነህ የሚል ነው፤ □□□ጸ□ም ዓይነት ከዚህ በፊት በዓለም □ሪ□ ታይቶ የማይታወቅ ነው፤ □ፌር ሜዳውም ያልተወሰነና ዓለምን በሙሉ የሚያጠቃልል ነው፤ □ፌር መሣሪጸ□ም እንደ ሰማይና እንደ መሬት የተለያየ ነው:: የአሜሪካና □እስራኤል የጥቃት መሣሪያ ዘመኑ ጸስ□ነው ደፍጥጦ የሚያነድ ነው፤ የተቃዋሚዎቹ የጥቃት መሣሪያ የሰው ልጅ ሕይወት ነው:: ከሁለቱም ወገን በየሳምንቱ ብዙ የሰው ሕይወት እየጠፋና ብዙ ንብረትም እየወደመ ነው:: ከሁለቱም በኩል በግልጽ አይሎና አመዝኖ የሚታየው ርኩስ መንፈስ እንጂ ቅን ወይም ቅዱስ መንፈስ አ□□ለም::

በአለፈው የፈረንጆች ምዕተዓመት ተከብረው የቆዩ ቁምነገሮች □□ተሻሩ ናቸው፤ የአንድ አገር ሉዓላዊነት በኃያላኑ ፈቃድ ብቻ የሚገኝ ሆኖአል፤ □□□ላቪጸ፣ አፍጋኒስታን፣ ኢራቅ የደረሰባቸውን እናውቃለን፤ በሰሜን ኮሬአና በኢራን፣ እንዲሁም በሶርያ ላይ የሚሰነዘረው ዛቻና ያንዣበበውም ስጋት ይህንኑ የሚያመለክት ነው:: የመረጣችሁትን መሪ ለውጡ የሚል ትእዛዝ ለአንድ ሕዝብ ማስተላለፍ በአሜሪካ ተጀምሮ አሁን አልቃይዳም የራሱን ትእዛዝ እያስተላለፈ ነው:: በአጠቃላይ ሲታይ በብዛት ሰዎችን መግደልና ንብረትንና የልማት መዋቅሮችን ማውደም የጉልበተኞች ብቻ ሳይሆን የደካሞችም ዘዴና መብት እየሆነ ነው:: የመንፈስ ልዕልና እንኳን በዓለማዊው ክፍልና መንፈሳዊ በሚባለውም ክፍል ክፉኛ ዘቅጦአል:: አካላችንን ብቻ ሳይሆን ነፍሳችንንም ለገንዘብ የምንሸጥበት ጊዜ ነው፤ የሰው ልጅ ኩራትና ክብር ዋጋ አጥተዋል:: ዓለማችን ለእኔ ይህንን ይመስላል፤ መናጢ ደሀዎችና ደካሞች ሆነን ያለነው እዚህ ዓለም ውስጥ ነው::

ያለንበት የዓለም ሁኔታ በአጠቃላይ ለጭቆና አገዛዝ የማይመች የሚመስል ዝንባሌ ቢኖረውም ኃያላኑ የጭቆና አገዛዞችን በአሽከርነት ለማሳደርም ዝንባሌ እንዳላቸው □□ጸል:: የምዕራባውያን ዋናው የሽብርተኞች ችግር ከጭቆና አገዛዝ ጋር ያላቸው መቆራኘት መሆኑን ገና የተገነዘቡት አይመስልም፤ የጭቆና አገዛዝ እስካለና ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል እስከታፈነ ድረስ ዓመፅና ሽብርተኛ ነት ይኖራል፤ የዓመፅና የሽብርተኛ ነት ኢላማም ከጭቆና አጋዛዙ በስተጀርባ ያለውን ድጋፍም እንደጠላት እየቆጠረ ማጥቃቱ የማይቀር ይሆናል:: አሜሪካ የሽብርተኞች ኢላማ የሚሆንበት ሌላ ምክንያት አለ ብዬ አላምንም:: የአሜሪካ □ሪካዊ ተልእኮዎች - ነፃነት፣ የሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነት ወይም ዴሞክራሲ፣ ትክክለኛ ፍትሕና የንብረት ማፍራት መብቶች ለሰው ልጆች ሁሉ የሚበጁ ቢሆኑም የአሜሪካ መንግሥት የማያወላውል አቅዋም ሆነው የውጭ ግንኙነት መመሪያው አላደረጋቸውም፤ እንዲያውም የአሜሪካ መንግሥት በተለያዩ ምክንያቶች የጨቋኞች ወዳጅና □ፉ□ እየሆነ ይገኛል:: ችግሩ □ህ □መስለኛል::

በምዕራባውያን ሕዝቦችና ከሌሎቻችን መሀከል ያለው ልዩነት እየገዘፈና እየጠለቀ በመሄድ ላይ ነው:: ሌሎቻችን በአራት ሺህ □መታት ያልደረሰንበትን እነሱ በአራት መቶ አልፈውት መሬት እየጠበበቻቸው ወደ ሕዋው እየመጠቁ ነው፤ □ኛ አህያ እየነዳን በቀን ሰባት ኪሎሜትር ሰንገሰግስ እነሱ በሰዓት ብዙ ሺህ ኪሎሜትሮች በመንፈላሰስ □□ተ፺□ ነው፤ □ኛ ጉልሁንና ዕዙፉን ነገር ማየት ሲሳነን □ነሱ በዓይን □ማ□ታየውን ሁሉ እያዩና □□መረመሩ ነው፤ □ኛ እነሱ □ሥሩትን መሣሪያ እየገዛን ስንክሳከስና ሞትን ስናነግስ እነሱ የሕይወትን ሙሉ ጣዕም እየተደሰቱበት ነው፤ □ኛ በ□ባቡ በአገራችን ውስጥ አብሮ መኖር ሲያቅተን እነሱ ሰፊውን ዓለም በግድም በውድም አገራቸው እያደረጉት ነው፤ እኛም ያጠፋነውን አገራችንን እየጠላን ወደነሱ አገሮች መሰደዱን ባህላችን አድርገን ይዘነዋል:: ገና ላልተሰደድነውም ቢሆን ከአገዛዙ ሥርዓት ጀምሮ እስከ ግብረ-ሠናይ ድርጅቶችና ማኅበሮች የምንንቀሳቀሰው በእነሱ ችሮታ ነው:: ከእነሱ ችሮታ ውጭ ያለን ህልውና ዋስትና የለውም:: እንግዲህ ጥያቄው ምን አለን? ብቻ አይደለም፤ ምንድን ነንም? ነው::

## 2. □□ለምና □አካባቢ ሁኔ□ በ□ኛ ላ□ ጸለ□ ተ□ክኖ

የኢትዮጵያዊነትን ህልውና □ሚ□ታተነው የውስጥ አመራር ብቻ ሳይሆን የውጪም ነው፤ □ሪ□ ጠባሳን ይተዋል፤ □ተለጸ□ የአውሮፓ የቅኝ ግዛት ኃይሎችን በተለያየ ጊዜ የኢትዮጵያ አልበገርነት አሳፍሮአቸዋል፤ አሜሪካም ቢሆን ይህንኑ አልበገርነት አይቶአል፤ እንዲሁም ቱርክ፣ ግብፅና አረቦች በተለያየ መንገድ የኢትዮጵያዊነት አለመበገር የተረዱበት ሁኔታዎች አጋጥመዋቸዋል:: ጎረቤቶቻችን ከሆኑት ጋር ግን የሚያያይዘን □□ምም፣ □ባህልም ማንነትም በሁለታችንም ላይ እንደቀረ አያጠራጥርም፤ አንዱና ዋናው ማንነተም እስልምና ነው:: እስልምና እንደሃይማኖት አረብ የሆነውን ያህል ኢትዮጵያዊም ነው:: ከክርስትናና ከእስልምና በፊት ኢትዮጵያዊነት ከአይሁድነት ወይም ቤተ እስራኤልነት ጋር ግንኙነት ነበረው:: በእኔ አስተያየት አይሁድነትም፣ ክርስትናም እስልምናም በተለያየ ጊዜ ኢትዮጵያዊነትን ለመተካት ሞ□ረ□ል፤ አንዳቸውም አልሆነላቸ□ም፤ ኢትዮጵያዊነትን በመተካት ፈን□ ሁሉም ኢትዮጵያዊነትን ተጎናጽፈው ኢትዮጵያዊ ሆኑ:: ኢየሩሳሌም ለሦስቱም ሃይማኖቶች ቅድስት መካን የመሆንዋን ያህል ኢትዮጵያዊነትም ከዚያች መሬት ታሪክ ተካፋይ ነው::

ሦስቱም ሃይማኖቶች ከኢትዮጵያ □□ ምእመናን አሉአቸው፤ ስለዚህም ሃይማኖቶቹ ከኢትዮጵያና በሌሎች አገሮች መሀከል እንደ ድልድይ ሆነው በማገልገላቸው፣ ሰዎች፣ ሃሳቦችና ባህሎች ተዛምደዋል:: ዛሬ ግን አይሁድነት ኢትዮጵያዊነትን አውልቆ እስራኤላዊነትን ለብሶአል፤ □ህ ሁኔታ ከሌላው የስደት ጎርፍ ጋር ተዳምሮ ኢትዮጵያዊነትን የማራቆቱ □ዞ መ□መሪጸ እንደሆነ አድርገን ልናየው የምንችል ይመስለኛል፤ ከዚያም በላይ የቤተ እስራኤል እስራኤላዊነት በእስልምና ኢትዮጵያዊነት ላይ ምን ተጽእኖ ሊያስከትል እንደሚችል አናውቅም፤ ክርስትናም በጎሠኛነት እየተተራመሰ የኢትዮጵያዊነት የክብር ልብሱ እየተቀዳደደበት ነው፤ እስካሁን ድረስ ጎሠኛነትን ተጋፍጦ በቆራጥነት የተቋቋመው እስልምና ብቻ ነው:: በአሁኑ ጊዜ ከእስልምና ወይም እንደሚባለው የእስልምና አክራሪዎች ጋር ምዕራባውያን በያዙት ግብግብ ውስጥ የኢትዮ□ጸን እስልምና ለማስገባት የሚፈልጉ አይጠፉም:: ስለ□ህም በ□□ ተ□እኖ ተገፋፍቶ የኢትዮጵያ □ስልምና ኢትዮጵያዊነትን ያዳክማል አገሪቱንም ለአደጋ ያጋልጣል የሚል ስጋት ይሰማል፤ አገዛዙ ከሶማልያው አል ኢትሀድ ጋር □ሚጸ□ር□□ ፅብፅብ በ□ህ በማሳበብ ነው:: እንዲህ ያለው የግጭት ምክንያት የኢትዮጵያን እስልምና ኢትዮጵያዊነት እንዳይመርዘው መጠንቀቅ □ሚጸስ□ልፅ □መስለኛል:: የክርስትና ኢትዮጵያዊነት በውስጥ አመራር ምክንያት እየተዳከመ ባለበት ጊዜ የእስልምና ኢትዮጵያዊነት ደግሞ በውጭ አመራር ምክንያት ቢዳከም በኢትዮጵያዊነት ላይ የሚደርሰው ጉዳት እንደሚባባስ በበኩሌ አልጠራጠርም:: በገንዘብ □□ተ□ለሉ ለምዕራባውያን ሎሌነት ማደር ለአገዛዙ የአጭር ጊዜ ጥቅም የሚያገለግል ቢሆንም ለኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ ጉዳትን ሊያስከትል ይችላል::

## 3. ከ□ት ተነስተን ጸለንበት □ረስን?

የአፄ □□ለ ሥላሴ አገዛዝ ለ□ኛ በጊዜው ወጣቶች ለነበርነው በአጉል ባህል □ተተበተበ፣ ኢ-ፍትሃዊ የመሬት ስሪት የሰፈነበት፣ ኋላቀርና አዝጋሚ ነበር:: ከሞተ ሠላሳ □መታት የሆነውን ሥርዓት ከዚህ በላይ አልወቅስውም:: ሆኖም ከጊዜው ጋር መሄድ ስላቃተውና □1953 □□በር □በኛ ዓመፅ ምንም ሊያነቃውና ሊያስተምረው ባለመቻሉ መጥፎ አወዳደቅ አጋጠመው:: ደርግ ከነትንሽነቱና ከነጭካኔው የዘውዱ አገዛዝ □ልህ ውጤት ነው::

የዘውዱ አገዛዝ ለኢትዮጵያ አጠቃላይ እድገት ያበረከተው አስተዋጽኦ በጣም ትልቅና ከዚያ ወዲህ ከመጡት ጋር ሲወዳደር

የማይችል ነው፤ በተለይ በሦስት ዓላማዎች ላይ በአጭሩ □□□·□ አገዛዙ ያበረከተውን አስተዋጽኦ ላመልከት፤-

- *በመ□መሪያ፣* በአንድነት ላይ በተለይ ኤርትራን ወደእናት አገርዋ ለመመለስ የተደረገውን ተጋድሎ አምባሳደር ዘውዴ ረታ ምስጋና ይድረሰውና በቅርብ ለማወቅ ችለናል፤ የዛሬውም የኤርትራ ችግር በዚያን ጊዜ የተፈጠረ መሆኑን ተገንዝበናል፤
- *ሁለተኛ፣* የመሬት ስሪቱን ትተን በእርሻ በኩል □ተ□መረ□· እድገት ቢቀጥል ዛሬ ኢትዮጵያ ራስዋን ከመቻል አልፋ የተለያዩ የ□ርሻ ምርቶችን ለዓለም ገበያ ማቅረብ የምትችልበት ደረጃ ላይ ትደርስ ነበር የሚል እምነት አለኝ፤
- *ሦስተኛ፣* የዘውድ አገዛዙ በትምህርት በኩል ኢትዮጵያ ራስዋን ወደምትችልበት ደረጃ አድርሶአት እንደነበረ ሁላችንም የምናውቀው ነው።

የትምህርቱን ጉዳይ ትንሽ ዘርዘር አድርጌ ልገልጸው □□ልፋለሁ፤ አፄ ኃይለሥላሴ ራሳቸው ከየሄዱበት ልጆች በመኪና እያስጫኑ በየትምህርት ቤቱ በአዳሪነት ያስገቡ ነበር፤ □ህ ክ□ል ባይኖር ብዙዎቻችን የዘመናዊ ትምህርት በርም አንደርስም ነበር፤ እንደማስታውሰው በተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት በአዳሪነት ከገቡት ውስጥ ለምሳሌ ከኦጋዴን ሶማሌዎች፣ ከሐረር አደሬዎች፣ ከጎጃም፣ ከጎንደር፣ ከትግራይ፣ ከሲዳሞ፣ ከአርሲ፣ ከኤርትራ፣ ከወለጋና ከአዲስ አበባም ዙሪያ የመጡ ነበሩ፤ ፍትሐ ነገሥት '*በፍትሐሰ ኢይ ትኴነን ወልድ በኂጋየ አቡሁ ወኢአብ በአበሳ □ልዐ*' 'ልጅ በአባቱ ወንጀል ወይም አባት በልጁ ወንጀል አይከሰስም' ያለውን በመከተል የታወቀው ከሃዲ □□ይለ ሥላሴ ጉግሳ ልጅና የአርበኛ□· ወመ□ኛ የበላይ ዘለቀ ልጆች ነበሩ። የተፈሪ መኮንን ተማሪዎች በዐመጽንበት ጊዜ 'ከየትም ለቃቀመን አምጥተን' በማለት ንዴታቸውን የገለጹት ለዚህ ነበር፤ የተናገሩት እውነት ቢሆንም እኛን ማስከፋቱ አልቀረም፤ ለዚህም ነው ማቴዎስ ጥግነህ የሚባል ተማሪ 'ጃንሆይ አባቶቻችን □□ስ ይከፍላሉ!' ያላቸው።

ይህ ባህላዊ አገዛዝ ከውስጥም ከውጭም ተቀጣጣሪ ኃይሎች ነበሩበት፤ ከውስጥ ኅሊና፣ ከውጭ እግዚአብሔርና ይሉኝታ ነበሩበት፤ ሽማግሌዎችም ነበሩ፤ በተፈ ማሪም አፄ ኃይለ ሥላሴ ብቻ ሳይሆኑ አሽከሮቻቸውም ጭምር ለየራሳቸው ክብር የሚሳሱ ነበሩ፤ ስለ□ህም ከውስጣቸውም ከውጭም የሚሰሙት ድምፅ ነበረ። ሆኖም አገዛዝ መማር አይችልምና የ1953 □ስዒረ መንግሥት ሙከራ አገዛዙን ሳ□ለ□·□□· ቀረ።

በእኔ ግምት የአፄ ኃይለ ሥላሴ አገዛዝ በኢትዮጵያ ዘመናዊ ትምህርትን በማስገባትና በማስ□ፋት በኩል ወደር የሌለው እርምጃን አሳይቶአል፤ ትምህርት በአጠቃላይና የከፍተኛ ትምህርትም በር ለማናቸውም ችሎታውን ላሳየ ደሀ ክፍት ነበር። የልዑላን፣ የመሳፍንትና የመኳንንት ልጆች ከደሀው ልጅ ጋር አብረው □□ተማሩ አደጉ። እ.ኤ.አ. በ1951 'ላ□□' የሚባለው መጽሔት ኢትዮጵያ አንድ መሀንዲስ እንኳን የሌላት ደሀ አገር ነች ብሎ መፃፉ እንዴት እንዳናደደኝ አስታውሳለሁ። ዓ ናው ነገር በዚያው ዓመት የከፍተኛ ትምህርት ተጀመረ። ያለምንም ጥርጣሬ የአፄው መንግሥት በትምህርት በኩል ኢትዮጵያን ገፍቶ ወደሃያኛ□· ምዕተ ዓመት አስግብቶአት ነበር ለማለት ይቻላል። ይህ βጦር ትምህርትም ቢሆን እውነት ነበር፤ በሐረር አካዳሚ፣ በደብረ ዘይት አየር ኃይልና በምፅዋ □ባሕር □□ል የነበረው የመኮንኖች ሥልጠና ሁለገብና በጣም ከፍተኛ ነበር። ኢትዮጵያ ከራስዋ ልጆች አልፋ የብዙ አፍሪካ አገሮች ወጣቶችንም በየመስኩ ታሰለጥን ነበር፤ ከነዚህ መሃል በየአገሮቻቸው ሚኒስትሮችና አምባሳደሮች የሆኑ ነበሩ።

በትምህርት የተደረገውን ከፍተኛ እርምጃ በገሃድ የሚያሳዩ ጥቂት መሥሪያ ቤቶች ነበሩ፤ ኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ የኢትዮጵያ ቴሌኮሙዩኒኬሽን፣ የመብራት ኃይል፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክና ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ በኋላ የቀዳማዊ □□ለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ። በዘመኑ እነዚህ ድርጅቶች ከየትም አገር ተመሳሳይ ድርጅቶች ጋር ተ□□□ረ□· □ማጸሳ□ሩ ነበሩ። □ሬ እነዚህ ድርጅቶች ያሉበትን ሁኔታ እንድነግራችሁ የምትፈልጉ አይመስለኝም።

የአፄ አገዛዝ ለትምህርት ይህንን ያህል ትኩረት ቢሰጥም የትምህርትን ባሕርይ ለመገንዘብ አልቻለም ነበር፤ በመሠረቱ መማር መለወጥ ነው። የተማሩ ሰዎች በተማሩት መጠን ይለወጣሉ፤ □ዓ ራ□ ነጠቅ መለወጥ ሳይሆን ጥልቀት ያለው ለውጥ ማለቴ ነው። በተለወጡት መጠን አካባቢያቸውን ለመለወጥ □□ልፋሉ፤ አካባቢውን ወደ ተሻለ ሁኔታ ለመምራትና ለመለወጥ የሚደረገውን ማናቸውንም □ርምጃ የአገዛዝ ሥርዓት አይፈቅድም። ስለ□ህም βአስተዳደርና በልማት በኩል የተማረው □□ል □ተመኘውን ያህል መራመድ አልቻለም፤ በአገዛዙና በተማረው ኃይል በኩል ቅራኔው ሰፊና ጥልቅ □የሆነ ሄደ። በዚያን ጊዜ ኢትዮጵያ በአፍሪካ ውስጥ የተሻለ ደረጃ የነበራት አገር በመሆንዋ ያንን ደረጃ መጠበቅ ብቻ ሳይሆን እንድትገሰግስና ለሌሎች አርአያ እንድትሆን የዘመኑ ወጣት ምኞት ነበር። ኢትዮጵያ ለአፍሪካ ብቻ ሳይሆን ለጥቁሩ ዓለም የነፃነት ጮራና □ተስ□ አርአያ ሆና እንደኖረች ሁሉ በኢኮኖሚውም

በኩል የከበረችና የበለጸገች አገር እንድትሆን ከፍተኛ ጉጉት ነበር:: ነገር ግን የኢትዮጵያ እድገት የኤሊ ጉዞ ሆነበት:: የአገዛዙ ትልቁ ድክመት ትምህርትን ለማስፋፋት ያደረገውን ጥረት ያህል የትምህርትን ውጤት ለመቀበል አለመቻሉ ነበር::

በመጨረሻም ይህ ባህላዊ አገዛዝ ሲወድቅ ኢትዮጵያ ያልፍላ□ል፣ □እድገት ግስጋሴዋ ይጣደፋል ተብሎ ነበር:: ነገር ግን አገዛዙ ሥልጣንን ለብቻው ጨብጦ በአንድ ሰ□ እጅ ለመቋጠር ሲል ሰዎች እንዲሰባሰቡና እንዲደራጁ፣ ሀሳባቸውንም በይፋ እንዲገልጹ የማይፈቅድ በመሆኑ አገዛዙም ሕ□ቡም በ□ ሌ □በታች መኮንኖች ተ□ለ□ና የሳንድኸርስትና የሳን ሲር ምሩቅ ጄኔራሎች በነበሩበት አገር ሻለቃዎችና የበታች ሹማምንት ነገሡባት:: ስለዚህም የባሰና ለሰው ሕይወት ምንም ዋጋ የማይሰጥ የጭካኔ አገዛዝ ተተካ፣ ስደት የኢትዮጵያውያን ባህል ሆነ፣ የትምህርት እድገት በጥራዝ ነጠቅ ማርክሲስት ሌኒንስት እምነት ቆረቆ□፣ ተጀምሮ የነበረው ከፍተኛ □እርሻ እድገት እንቅስቃሴ ተገታ፣ ዓ ሩምባ እየነፋ መግደልና መንጠቅ የጊዜው ባህል ሆነ::

በደርግም ዘመን ልክ እንደዘውዱ አገዛዝ ሥልጣን በአንደ ሰው □ፀ ተቋጥሮና ሕዝቡ በጭካኔ ታፍኖ በማን አለብኝነት ግፉን □□ተቀበለ እስቲያንገሸግሸው ድረስ ቆይቶአል፣ በመፌ ረሻም 'የነቃ፣ የተደራጀና □ታጠቀ ኃይል ያሸንፋል፣' በሚለ□ □ራሱ □□ርዕ መፈክር መሠረት ተገፍቶ ገደል ገባ፣ ደርግን የተካው ወያኔ ከጫካ የወጣ ጀሌ ነው፣ የአፄ ኃይለ ሥላሴ ጄኔራሎች በበታቾቻቸው እንደተበለጡ ሁሉ ደርግም ከጫካ በወጡ ጀሌዎች ተበለጠ:: ከአፄ መውደቅ ጋር የተጀመረው የቁልቁለት መንገድ ገና አላቆመም፣ ያለንበትን ሁኔ□ ስናስበው ይህንን ለመገንዘብ አዳጋች አይደለም::

## 4. ያለንበት ሁኔ□

በአጭሩ በነደፍሁላችሁ ርኩስ መንፈስ በሰፈነበት ዓለም ውስጥ እንገኛለን፣ ይህ ርኩስ መንፈስ ሩቅ አይደለም፣ □ሀነታችን፣ የምኞት ባሮች መሆናችን፣ የውስጣችን መንቃት ወይም መሰነጣጠቅ ርኩስ መንፈስን ከያለበት የሚጋብዙ ናቸው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላማዊና መከራን የሚችል ነው፣ እንደኛ ደግና ት□ዕስተኛ ሕ□ብ □ለም፣ ተዘረፍን ብለን ሳንቆጣ፣ ተጠቃን ብለን ሳንጮህ፣ ሕጋዊ ሥርዓት ተፋለሰ ብለን ሳንበሳጭ፣ የደሀውና የሥራ አጡ ለቅሶና ብሶት ሳይሰማን፣ ሁላችንም በዕለት ተዕለት የኑሮ ግዴታ ተጠምደን፣ ተጨንቀን ሳናስብ እንኖራለን:: የተማረው ያልተማረውን፣ ያልተማረው የተማረውን እየናቀው፣ ወጣቱ በሽማግሌው፣ ሽማዕሌ□ በ□□ቱ፣ ሀብ□ሙ በ□ሀ□፣ □ሀ□ በሀብ□ሙ፣ ገጠሬው በከተሜው፣ ከተሜው በ□□ሬ□ □ጸመካኝ፣ ጠመንጃ የነገተው ሌጣውን ቀንበር እያሸከመው፣ ትናንት ስንሰግድለት የነበረውን ዛሬ እያዋረድን፣ ነገ የምናዋርደውን ዛሬ እያከበርን የኑሮ ፅ□ታችንን (ማለት በልቶ ማደርን) ብቻ ዓላማ አድርገን እንኖራለን:: ስለነገው አንጨነቅም፣ ስለነገ የማንጨነቅበት ዋናው ምክንያት ነገን የሚያንፁትና የሚያቅዱት ጌቶች ስለሆኑ □ኛን አያገባንም፣ ስለነገ አለመጨነቅ የባርያ ባሕርይ ነው:: ስለዚህም ነገ የራሱን ጣጣ ይዞ ሲመጣ ራሳችንን ለአዲሱ ጣጣ ከማዘጋጀትና ጊዜያዊ የግል ጥቅማችንን ከማረጋገጥ ሌላ ለማሰብ ዝንባሌውም ፍላጎቱም የለንም:: 'ያለው ላይቀር ምን አታገለኝ' የሚል ፍልስፍና ነው መመሪያችን::

የአንድ አገር ሕዝብ የአገርና የሥልጣን ባለቤትነቱን ለማሳወቅና ለመታገል ካልተነሳ እንዴት ጸል□ለታል? ችግሩን ሁሉ በአገዛዝ □ጸመካኙ አምላክን፣ መላእክትንና ሰማክታትን በመማፀን ብቻ መፍትሔ በመጠበቅ ሁለት ሺህ □መታት ሊሞላን ነው:: ጸሎቱንም የሚያሳምርልን ልብ የለንም፣ ልባችን በክፋትና በጥላቻ፣ በቂምና በምቀኝነት የተሞላ ስለሆነ የልባችንን የሚያውቅ አምላክ የአፋችንን ጸሎት የሚሰማበት ጆሮ ያለው አይመስለኝም:: በቀን ብዙ □□ □ኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል እያለ የሚጸልየው ሁሉ የምህረትና የይቅርታ አቅዋም በሚያስፈልግበት ጊዜ አካሉ እየተንቀጠቀጠ አንደበቱ የበቀልን እሳት ይተፋል፣ እን□ን የቅርቡን የምዕተዓመታት ታሪክን እያስታወሰ ለበቀል ፌር □ሰብቃል:: ሰለ□ህ ለጸሎትም ቢሆን ልባችንን ንጽሕና □□□ለ□ል፣ አገራችን በመንፋሳዊነትም የከሰረች ነች:: መንፈሳዊነትን በሃይማኖ□ዊ ትርጉሙ ብቻ አንውሰደው፣ እኔ የምጠቀምበት ለእውነት፣ ለነፃነትና ለፍትህ፣ ለእኩልነትና በአጠቃላይ ክፋውንና በጎውን ለምንለይባቸው የኅሊና ተግባሮች ሁሉ ጭምር ነው::

በዚያ ላይ ጎመን በጤና በሚል ሰንካላ ፍልስፍና ተመርዘናል፣ ፍርሃት ወኔአችንን ገድሎ□ል፣ ኢትዮጵያውያን የምንላቸው □እውቀትና የሀብት ባለቤት የሆኑትን ብቻ ቢሆን እኔ በበኩሌ አገዛዙ የሚገባቸው ነው ለማለት አያዳግተኝም ነበር፣ ነገር ግን ከዘጠና በመቶ በላይ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በችግርና በችጋር እየተጠበሰ የሚኖር ነው፣ ለ□ሱ፣ በጭቆናና በብዝበዛ ሥር በችግር ተወልዶ በችግር ለሚሞተው አገዛዝ □ሩ ነው:: የሀብትና የእውቀት ባለቤቶች ምርጫቸው ብዙ ነው፣ ከተገነዘቡት ባላቸው መጠን ፅ□ታቸው ወይም ኃላፊነታቸው ከባድ እየሆነ ይሄዳል፣ ይህንን ፅ□ታ አለመቀበላቸው ካላቸው የምርጫ ብዛት ጋር በጭቆና ሥር መውደቃቸው የሚታዘንላቸው

አያደርጋቸውም:: ማኅበረሰቡ ከነዚህ ክፍሎች የሚጠብቀውን የአለኝታነት፣ የመከታነትና የአመራር በረከት ገና አላገኘም:: ለማኅበረሰባችን መንፈሳዊ ውድቀት አንዱና ዋናው መግለጫ የሀብትና □እውቀት ባለቤት የሆነው ክፍል ፅ□ታቢስነት ነው፣ ከተመቸውና በኢትዮጵያ መጠቀም ከቻለ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለግዴ□ መኖርን፣ ካልተመቸው በሌላ አገር ሄዶ መኖርን እንደአማራጭ ይዞ ያለ ነው:: በሌላ አነጋገር አንድ እግሩን በፈረንጅ አገር አንድ እግሩን በኢትዮጵያ አንፈራጥጦ የሚኖር ነው፣ እንደ አንድ አገር ሕ□ብ □በ□ኃኑ ስቃይና ብሶት እንዲጋባብንና እንዲሰማን ኀሊናችን አስገድዶን ኢትዮጵያ ለ□ኛ □□□ራም እንጀራ ምንጭ ብቻ ሳትሆን □ኛም □ርስ□ እንጀራ ምንጭ መሆናችንን መቀበል ገና አልቻልንም:: በራሳችን ዓይን ያለውን ጉድፍ ሳናወጣ አዛዡ ላይ □ታችንን መጠቆሙ ብቻ የትም አያደርሰንም::

የመንፈስ ደካሞች በመሆናችንም አሁንም የምንኖረው እንደተለመደው ከ□ኛ ቁጥጥር ውጭ በሆነ የአገዛዝ ሥርዓት ሥር ነው:: የአገዛዝ ሥር□ቱ መሠረ□ዊ ባሕር□ ሁሉንም ነገር ለብቻ በሞኖፖል መያዝና ሁሉንም ነገር መቆጣጠር ነው፤ የአገር ሥልጣንን ለብቻው፣ የሀብት መሠረት የሆነውን መሬትን ለብቻው፣ የሕዝብ የዜና ማሰራጫዎችን ለብቻው፣ የአገዛዝ ሥርዓቱ ራሱ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ዓ□ኛ ሆኖ ሳለ የአገሩን ባለሀብቶች በጥገኝነት እየፈረጀ ለማሳፈርና እድገታቸውን ለመግታት የሚሻው ጥገኝነትንም በሞኖፖል ለመያዝ □መስላል:: በ□ጸ ላ□ ሥር□ቱ የዜና ማሰራጫ፣የዜና ወኪል፣ የንግድና የኢንዱስትሪ፣ የቲአትር፣ □ማስታወቂያና የማሳተሚያ ድርጅቶች ቢያንስ የእጅ አዙር ባለቤት ሆኖ ሌሎች ባለሀብቶች □ማጸ□ትን ዕድልና ድጋፍ በማግኘት ከውድድር ውጭ ያደርጋቸዋል፤ በማኦኢስቶች አነጋገር ይህ □ቢሮ□ራሲ.ጸዊ ካ□ታሊዝም ነው::

ኢትዮጵያውያን ሁሉ ባይስማሙበትምና አፄ □□ለ ሥላሴ 'ለምንወደው ሕዝባችን' እንዳሉት ባይሆንም፣ ለምንገዛቸው ጎሣዎቻችን በሚል መንገድ የተሰጠና መነሻ ሆኖ ሊያሠራ የሚችል ሕገ መንግሥት ለወጉ አለ:: ዛሬ ጥያቄው ሕገ መንግሥቱ ዓሩ ነው? ወይስ መጥፎ? የሚል አይደለም፤ ጥያቄው ሕገ መንግሥቱ ነፍስ አለ ወይ? ነው:: አገዛዙ ራሱ በገዛድ ያለምንም ሀፍረት የህገ መንግሥቱን ጥርስ ሲያረግፈው እያየን ነው:: እንዳሁኑ የአገዛዝ ሥርዓት ፍትሕን ሙሉ በሙሉ በቁጥጥር ሥር ያደረገ ከዚህ በፊት አል□□ም:: በአሁኑ አገዛዝ ደሀዎች፣ ሴቶችና ወንዶች ልጆች ከየመንገዱ ሌሊት □□ተለቀሙ ከከተማ ውጭ ስንት ጊዜ ለጅብ ተጣሉ? በቅርብ አንዱን ጋዜጠኛ እንደእባብ ራሱን ቀጥቅጠው ከድልድይ ወደ ወንዝ ወረወሩት፤ ዛሬ በሕግ አምላክ ማለት ትርጉም የለውም:: ስንት ሺህ ሰዎች ናቸው ፍርድ ቤት እንኳን ሳ□ቀርቡ አሥር ዓመት ያለፋቸው? ስንት ሙቶ ሰዎች ናቸው ተገድለው ደማቸው ደመ ከልብ ሆኖ የቀረው? ስንት ሰዎች ናቸው በጥርጣሬ ብቻ በእስር ቤት የሚማቀቁት? ስንት ሺህ ሰዎች ናቸው ከኤርትራ ተፈናቅለው ከአሥር ዓመት በላይ ከአን□ መ□ለጸ □□ሌላ መ□ለጸ □□ተባረሩ የሚኖሩት? ስንት ልጆች በ□መ□ለጸ□ □□ተ□ለዐ በ□ባቡር መንገዱ ላይ ያድጋሉ? ስንት ሺህ ሰዎች በኤርትራ ጦርነት ምክንያት ከየቤታቸው ተፈናቀሉ? ስንት ሺህ ሰዎች በጎሣ ምክንያት ተፈናቅለው በችግር ይኖራሉ? አሁን ደግሞ ስንት ሺህ ሰዎች ከጂቡቲ ተፈናቅለው መጥተዋል? የመንም ኢትዮጵያውያንን እያባረረች ነው □ባላል፤ እነዚህ ሰዎች ሁሉ አገርና መንግሥት አላቸው? ወገን አላቸው?

አሁን ያለንበት የአገዛዝ ሥርዓት □□ርፅ □ባሕር□ ታናሽ ወንድም ነው፤ በደርግና በወያኔ አገዛዞች መሀከል ያለው ልዩነት የጌቶቻቸው የባሕርይ ልዩነት ብቻ ነው:: የደርግ አገዛዝ አፍአዊ ገጽታውን የሶሺያሊስት ቀለም እንዲቀባ የተገደደውን ያህል፣ በወያኔ አገዛዝም አፍአዊ ገጽታውን □□ሞ□ራሲ ቀለም እንዲቀባ ተገደደ:: ጉልቻውና ቀለሙ ተለ□□□ እንጂ ማገዶውና የሚጠበሰው ያው ነው:: የበላውና የጠገበው ሲሄድ የራበውና ሁሉ-ብርቁ □ተካል፤ በሁለቱም ላ□ ቢሆን ራስን መጠራጠር፣ በጎ ፈቃድና መንፈሳዊ ወኔ የለም:: በሁለቱም ላይ ጎልቶ የሚ□□ሁ በተለያየ መንገድ ከእነሱ የሚበልጡ ሰዎች በአገር እንዳይኖሩ ነው:: ወደ አውሮፓም ሆነ ወደ አሜሪካ፣ ወደ አውስትራሊያም ሆነ ወደ አረብ አገሮች ስደትን የኢትዮጵያውያን ባህል ያደረጉ አገዛዞች ናቸው::

## 5. የያዝነው አቅጣጫ የት ያደርሰናል?

ከተለያየ የትምህርትና የሥራ መስክ የመጡ ቢሆኑም ከዚህ በፊት የተናገሩት ሁሉ በአንድ ነገር ላይ □ስማማሉ፤ - አሁን በተያዘው መንገድ መቀጠል አንችልም:: የያዝነው መንገድ ወደ 'ከፋ ዕድል'፣ □□ 'መዓት'፣ □□ 'ውድቀት' የሚያመራ መሆኑ ተገልጾአል:: ለእኔ የአዘቅቱ መንገድ የሚታየኝ እንደሚከተለው ነው፤ በሽምበቆ አጥር የተለያዩና የሚተራመሱ ጎሣዎችን ጭኖ የሚከንፍ ባቡር □□□ኛል፤ ነጂው መትረየሱን ይዞ ፊቱን አ□ሮ □ተቀመ□□ ወደሚነዳበት አቅጣጫ ሳይሆን ወደተሳፋሪዎቹ ነው፤ ተሳፋሪዎቹ የሚያዩት ወደፊት ነው:: ነጂው የሚያየው ወደኋላ ነው፤ ስለ□ህም ነጂው ገደሉን ስለማያይ ይበልጥ

የሚያስፈራው የተሳፋሪዎቹ ትርምስ ነው፤ ተሳፋሪዎቹን የሚያስፈራቸው የሚታያቸው መትረየስና ገደል ነው፡፡ በባቡሩ ውስጥ ያሉ ተሳፋሪዎች ሁሉ በባቡሩ ፍጥነት ላይም ሆነ አቅጣጫ ላይ ምንም ዓይነት ቁጥጥር የላቸውም፤ የባቡሩ ነጂ ተሳፋሪዎቹ የሚያዩትን አያይም፤ እንዲነፅሩትም አይፈልግም፤ የነጂውና የተሳፋሪዎቹ አስተሳሰብ ለየቅል ነው፤ አይነጋገሩም፤ ተሳፋሪዎቹ በዝምታ ነጂው የማያየው ገደል ውስጥ ለመግባት ቆር□□ል፤ ባቡሩን አቁም ብለው ቢጮሁ መልሱ መትረየስ መሆኑን ጸ□ቃሉ፤ በ□ምታ አብሮ ገደል መግባት ነው፡፡ በዚህ አጣብቂኝና የፍርሃት ቆፈን ተይዘናል፣ ከተረዳንለት ነጂውም አጣብቂኝና የፍርሃት ቆፈን ውስጥ ነው፤ ነጂውና ተሳፋሪዎቹ ካልተነጋገሩ ባቡሩም፣ ተሳፋሪዎቹም፣ ነጂውም ከገደሉ ማምለጥ አይችሉም፡፡

እንግዲህ መሣሪያ የያዘውም □□ራል፤ መሣሪጸ ጸልጸ□□ም ይፈራል ማለት ነው፤ □ሁለቱም ጠላት አለመተማመንና መሣሪያው ነው፡፡ አለመተማመንን ሳናጠፋ መሣሪያውን ማጥፋት አንችልም፤ ሳንነጋገር አለመተማመንን ማጥፋት አንችልም፤ ልባችን ከቂምና ከበቀል ካልፀዳ ተነጋግረን መግባባት አንችልም፡፡ ባቡሩ እውር ድንብሩን እየሄደ ገደል የሚገባው ለዚህ ነው፡፡

□ባቡሩ ገደል መግባት የአደጋው መ□መሪጸ እንጂ መጨረሻ ይሆናል የሚል ግምት የለኝም፤ አደጋው የጎሣ ትርምስና የቂም መወጫ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ ለብዙ ምዕተ □መታት ወደኋላ ሄደን ከሌሎች የአፍሪካ አገሮች ጋር እንሰለፋለን፡፡ የያዝነው መንገድ ወደዚህ □ንደሚያመራ ለእኔ ግልጽ ነው፡፡ ይህንን የሚጠራጠር ትንሽ ያስብበት፤ ለሌሎች የተዘራው የጎሣ መር□ ባልታሰበበት መንገድ ሄዶ በኤርትራና በትግራይ ተወላጆች መሃከል የከፋ መልኩን ማሳየቱ የሚያሳዝንና የመርዙንም ጠምዛዛነት የሚያመለክት ነው፤ የዚህ ጦስም የትግራይ ተወላጆችንም በመከፋፈል ላይ ነው፡፡ አነግ ጎልቶ የሚ□□ ቢሆንም በሌሎች የኢትዮጵያ ክፍሎች በማቆጥቆጥ ላይ ያለ□ □ሥኛነት ጉዳዩን ለሚከ□ተሉ ሁሉ ግልጽ ነው፡፡ በጎሠኛነት ተኮትኩተው ያደጉ ልጆች □□□ረሱ ነው፤ አንድ ትውልድ ሊሆን ምንም ያህል አልቀረውም፡፡ ብዙዎቻችንን የሚያሳስበን የደህነቱና የችጋሩ ጉዳይ ነው፤ የኢትዮጵያን ህልውና ጉዳይ ባንረሳውም አደጋውን ላለመቀበል አእምሮአችንን የምንጋርደው ይመስለኛል፤ ጭንቅላታችንን አሸ□ □ስዓ ቀብረን የምንፈልገውን መመኘቱ ብቻ አቅጣጫችንን አይለውጠውም፡፡ እኔ የማውቃትና አገሬ የምላት ኢትዮጵያ አሁንም በከፊል የለችም፤ በያዝነው መንገድ ከቀጠልን ደግሞ ያሁንዋም ኢትዮጵያ 2020 የምትደርስ አይመስለኝም፡፡ በያዝነው መንገድ ከቀጠልን የብዙ የአፍሪካ አገሮች ሁኔ□ □ስዓ መግባት የማይቀር ነው፤ ኢትዮጵያ የምትባል አገር ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን በጥያቄ ምልክት ውስጥ መግባትዋ የሚቀር አይመስለኝም፤ ከዘመነ መሳፍንት የባሰና አስከፊ ሁኔታ እንደሚያጋጥመንና በሆነ ባልሆነው መከሳከሳችን ይቀራል ብዬ አልገምትም፡፡

የወደፊቱ ግጭት ከአሁን በፊት ከለመድነው በጣም የተለየ ይሆናል፤ እስከዛሬ የምናውቀው ግጭት በአፈንጋጭ የማኅበረሰቡ ክፍልና በአገዛዙ መሀከል ነበር፤ ቀ□ም ሲል እንደተናገርሁት ደርግ ራሱ ባ□□□ 'የነቃ፤ የተደራጀና □□□ቀ ያሸንፋል፣' በሚለ□ ሕፅ ወደቀ፤ ወያኔም ራሱ የጠነሰሰውና ሕፋዊ ጸ□ረ□□ □ሥኛነት የሚፈጥረው ግጭት እንደበፊቱ በአገዛዝና በአፈንጋጭ ቡድን መሀከል ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ጎሣዎችም መሀከል ይሆናል፡፡ በ□ሥኛነት ተኮትኩቶ ያደገ ትውልድ በማኮብኮብ ላይ ነው ብያለሁ፡፡ ዛሬ በትግራይና በኤርትራ ተወላጆች መሀከል ያለው ስሜት ነገ በሌሎች መሀከል ይከሰ□ል፡፡ በተነጠቁት መሬት የተነሣ ወሎና ጎንደር ውስጥ ያለው የታፈነ ንዴት ቀላል አይደለም፤ አፋር ተከፍሎና ታፍኖ አይኖርም፤ አነግ □□ተ□ፋ ነው፤ ኦጋዴን ለመገንጠል ይችላል የሚል ማደፋፈሪያ ተሰጥቶ□ል፤ ሌላ□ በ□□ራ□ እያብላላው ነው፤ የጎሣው ግጭት የሚፈጥረው ትርምስና መተላለቅ ከጀመረ በራሱ □□ል □□ተቀ□□ለ ስለሚሰ□□ ለማቆም አስቸጋሪ ይሆናል፤ ስለዚህም ሰላም ይኖራል ብዬ አልገምትም፡፡ አዘቅቱ የከፋና የኢትዮጵያ ሕዝብ በታሪኩ አይቶት □ማያውቀው ደህነትና ችጋር ጭካኔን □□□ለ□፤ በ□ሥኛነት ሞተር እየተነዳ፣ በጥላቻና በቂም እየታወረ ክፋት በገሃድ የሚወጣበት መተላለቅ ነው፡፡

በዚህ መተላለቅ ከአካባቢያችን የሚረዱን አይጠፉም፤ በአለፉት □መታት ከሶማልያና ከኤርትራ ጋር የተደረገው መዳማት፣ ከጂቡቲ ጋር የተከሰተው አለመግባባት፣ በአንድ በኩል ከአሜሪካ ጋር፣ በሌላ በኩል ከሱዳን ጋር የተደረገው ሽር-□□ □ሚከተሉትን ዓመታት ለኢትዮጵያ የሚመቹ አያደርጉም፡፡ እኔ እንደምገምተው ሁሉም የተነበየው አዘቅት ወይም መዓት አፋፍ ላይ በ1997 መፈ ረሻ እንደርሳለን፡፡ አዲስ ኢትዮጵያ የምትወለደው ከኤርትራ እስከ ቦረና ከጋምቤላ እስከ ጂጂጋ ሁሉም በአንድ ጊዜና በአንድ ላይ በሚሰማው የጭንቀት ምጥ ይሆናል፡፡ ሕገ አራዊት የሚያደርሰን እዚህ ነው፡፡ የሰው ልጅ አእምሮ ውስብስቡን የኑሮ ገመድ ሲገምድና ሲፈ□ □ኛ ገና ከቀላሉ የማስፈራራትና የጡንቻ ዘዴ አልወጣንም፤ በማስፈራራትና በጭቆና የጨቋኙም □ተፈ ቋኙም አእምሮ ደንዝዞ፣ መንፈስም ታምሞ፣ በደነዘዘ አእምሮና በታመመ መንፈስ ትርጉም ያለው ሥራ ለራሳችንም ሆነ

ለማኅበረሰባችን ለማበርከት አንችልም::

እንደምትገምቱት ይህንን መናገር ቀላል አይደለም፤ እስካሁን ድረስ ሦስት አገዛዞች በውርደት ሲወድቁ አይቻለሁ፣ የሁለቱ አገዛዞች መ□ሁ□ቅ በቅ□ሚጸ ታውቆኝ በአደባባይ ተናግሬ ነበር:: የአሁኑ አገዛዝ በዓይነቱ በጣም የተለየ ነው፤ ራሱን ለማረም በጊዜው ካልጣረ አወዳደቁም የተለየና አገሪቱንም የሚያጠፋ ለሆን ይችላል፤ ነገር ግን ባሕሩ እንዳለው ኢትዮጵያ የተአምር አገር ነች፤ አለቀላት ሲባል ነፍስ ዘር□ ትነሣለች:: እንደዚያ ከሆነ ደስታው የሁላችንም ነው:: በተአምር ባምንም እጆቻችንን አጣምረን በመቀመጥ ከአንዣበበው አደጋ እናመልጣለን ብዬ ግን አላስብም::

## 6. አደጋውን ለማስቀረት ምን ማድረግ አለብን?

ይህንን ጽሑፍ በማዘጋጅበት ጊዜ ከኘሮ□ሰር □ታቸው ኃይሌ በቅርቡ □ሚታተም መጽሐፍ ረቂቅ ደርሶኝ እያነበብሁ ነበር፤ ስለደቂቀ እስጢፋኖስ በአሥራ አምስተኛ□ ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ላይ የሆነውን ከግዕዝ የተረጎመው ነው፤ ከተጻፈ ስድስት መቶ ዓመታት የሆነው ነገር ሁሉ ዛሬም የሚሆን ነው፤ የሚያሳዝንም የሚያስደንቅም ነው፤ በሥልጣን ላይ ያሉት ሰዎች የሀሳብ ልዩነትን መቀበል የማይችሉ መሆናቸውና እንዲህ ያሉትን ሰዎች በተለየየ መንገድ ማሰቃየታቸው፣ የማሰቃያው መንገድም ብዛቱ እንዳለ ምንም ሳንለወጥ መቆ□ታችንን በግልጽ ያመለክታል::

ለእኔ እንደሚታየኝ አቃለልከው ካላላችሁኝ ታሪካዊ ችግሮቻችን ሁለት ብቻ ናቸው፤ አንደኛ፣ በረፀሙ ታሪካችን ውስጥ የምናየው በሕገ አራዊት መመራትን ነው፣ ከ□□ል □ተሻለ □መተ□□ሪጸ □□ አልፈጠርንም፤ የበላይና የበታች በመሆን ባለመብትና ባለግዴ□ እየተለየ ጌታና ሎሌ በመሆን አጉል መቻቻል እንጂ በእኩልነት ላይ ለተመሠረተ ግንኙነት የሚሆን ዘዴ አላገኘንም:: ሥልጣንን መግራት ሳንማር 1996 ደርሰናል፤ ሥልጣንን መግራት የሥልጡን ሕዝብ መታወቂያ ምልክት ነው፤ በሕገ አራዊትና በጉልበት እየተገለባበጥን እንቃጠላለን:: የእድገትና የልማት አንዱ ምስጢሩ ሥልጣንን መግራት ነው፣ ሥልጣንን በእኩልነት ሕጋዊ ማድረግ ነው::

ሕገ አራዊትን መመሪያችን በማድረጋችን ነው በአጠቃላይ ባህላችን የነፍጠኛነትና የጀብደኛነት የሆነው፤ ጠመንጃ ተይዞ በፉከራና በሽለላ ታጅቦ፣ ጀግና፣ ገዳይ በመሆን ነው '□ኔ ያንተ አሽከር ያንተ ቡችላ' የሚባልለት፤ አሁን ደግሞ ማጅራት መቺ፣ አከርካሪት ሰባሪ ሆኖ በሕገ አራዊት ለሚያደናብረው ነው አሽከርነት የማያድረው፤ አሽከር ዛሬ ስሙ ተለውጦ ካድሬ ሆኖአል እንጂ እዚያው ነን:: በባህላችን ብዙ መሳፍንትና መኳንንት ስለነበሩ አሽከር ምርጫ ነበረው፤ ዛሬ ጌ□□ አንድ ብቻ በመሆኑ ምርጫም የለም፤ ዘመናዊነቱና ለውጡ እስከዚህ ድረስ ነው:: የምናየውና የምንሰማው ያንኑ የለመድነውን □ □ን እልህ ነው:: የጂቡቲው ኘሬዚደንት ጉሌድ ዲፕሎማሲያዊ ቋንቋውን ጥለው 'የኢትዮጵያና የኤርትራ ሰዎች ከሚገባው በላይ ቁጡና ጠበኛ'[1] ናቸው ብለው መናገራቸው በሕገ አራዊት ላይ የተመሠረተው አገዛዝ ድንበር አልፎ መታወቁን የሚያመለክት ነው::

ሁለተኛ□ ችግራችን ሥልጣንና ሕገ ኅልዮት አለመተዋወቃቸው ነው፤ ሕገ አራዊት አይሎ ነው እንጂ ሕገ ኅልዮት ለኢትዮጵያ ባዕድ ሆኖ አይደለም፣ □□ላስ□ዎቹን የዘርዓ ያዕቆብንና □□ል□ ሕ□□ትን ጽሑፎች ያነበበ ሁሉ እንደሚረዳው፣ አሁን ደግሞ ኘሮ□ሰር □ታቸው ለመጀመሪያ ጊዜ ከግዕዝ ወደ አማርኛ እየተረጎመ የሚያሳትማቸው መጻሕፍትም እንደሚያሳዩን ማሰብ በጡንቻ □□ተፊ □ለቀ □ብ□□ እንዲጠፋ ተደረገ እንጂ በአዲስ መንገድ ማሰብ የሚችሉ ሰዎች በ□□□□ ብቅ ብቅ ብለ□ እንደነበረ እናያለን:: የሀሳብ ልዩነት የማይፈቀድና ለከባድ አደጋ የሚዳርግ መሆኑ ቢያንስ ከአሥራ አምስተኛው ምዕተ ዓመት መነሻ ላ□ እንደጀመረና ለስድስት መቶ □መታት ቆመን እንደቀረን ያሳየናል:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ጦርነት ሲሉት ፈንቅሎ የሚወጣውን ያህል ለሰላማዊ ትግል አንድነቱን ቢያሳይ ኢትዮጵያን ከታሪካዊ ችግሮችዋ መገላገል ይቻል ነበር::

ከኤርትራ ጋር ለተደረገው የወንድማማች ጦርነት የሀብትና □እውቀት ባለቤቶች ያደረጉት ከባ□ አስተዋጽኦ የሚያስደንቅ ነው፤ በእነሱ አመራርም በብዙ ሺህ □ሚቆ□ሩ የኢትዮጵያ ወጣቶች ለባድመ ተማገዱ፤ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ስትገነጠል ግን ከዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በቀር የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጣውን ለማሳየት እንኳን አልሞከረም፤ ለሞት በቀላሉ እንነዳለን፤ ለሕይወት ግን በሰላም ለመ□□ል እንፈራለን፤ ዛሬም የባድመ ነገር የሚያንገበግባቸው ብዙ ናቸው፤ በአንጻሩ ደግሞ የአሰብ ጉ□□ የማያቃጥላቸው ብዙ ናቸው፤ የባድመ ተቆርቋሪ የአሰብ ተቆርቋሪው ንዴት የሚገባው አይመስልም፤ እንዲሁም ለዚያኛ□፣ ለቁጣችንም ሆነ ለትዕግስታችን ሚዛን የለንም፤ ይህ ሁሉ የሚየሳየው ሕገ አራዊት በሕገ ኅልዮት ላይ ያለውን የበላይነት ነው:: ይህ መለወጥ አለበት፤ □ኛ መለወጥ አለብን፤ □ኛ ራሳችንን

[1] አዲስ አድማስ ጋዜጣ ጥቅምት 21/96፣

ሳንለውጥ ምንም ነገር መለወጥ አንችልም::

ለጦርነት የምናሳየውን የጋለ ስሜት ለሰላማዊ ትግል አናሳይም፤ ሰላማዊ ትግል ወይም ፖለቲካ ገና አልገባንም፣ ደርግ ሰላማዊ ትግሉን ወደሶሺያሊስት የመደብ ትግል ለወጠው፤ መደብ በሌለበት አገር:: ወያኔ ደግሞ በልጅነት ጥበቡ የሰላሙን ትግል መሠረ□ዊ □ስ□ ልጅን አንድነት በሚቃረንና ወደ ድርድር በማይቀርብ የጎሣ ትግል ለወጠው:: የደርግ ሶሺያሊስት ትግል ሁሉንም ደሀ በማድረግ መፍትሔ ለማግኘት ይችል ነበር፤ ሁሉንም ሀብ□ም ለማ□ረፅ እስቲችል ድረስ:: የወያኔ እልህ ግን ከመበታተን ሌላ መፍትሔነት ያለው አይመስልም:: የሚደንቀው የጎሣ ትግሉ በእያንዳንዱ በአመራር ደረጃ ላይ ባለ ሰው ላይ የፈጠረውን የውስጥ ቅራኔ እንኳን መገንዘብ አለመቻሉ ነው:: እንኳን ራቅ ካሉ ጎሣዎችና በጣም በተቀራረቡትም በትግራይና በኤርትራ መሀከል መደባለቅ ችግር እየፈጠረ እናያለን:: መበታተኑም ወግና ሥርዓት ባለው መንገድ እንደማይሆን ባድመ እያስተማረን ነው፤ (ገና ጥንት አብርሃም ሊንከልን አንድ ቤት ውስጥ ሆነው ለመፈጸም ያልተቻለውን ውል ከተለያዩ በኋላ ያስቸግራል ብሎ ነበር፤) በደቡብም በየጊዜው የሚከሰቱ ግጭቶች የወደፊቱን ችግር እያመላከቱን ነው:: መበታተኑም ቢሆን ሰላማዊ ላይሆን ይችላል የሚል ስጋት አለኝ::

በሕገ ኀልዮት የምንመራ ቢሆን ለማናቸውም ዓይነት እድገትና ልማት የሕዝቡ የሥልጣን ባለቤትነት ወይም ደሞክራሲ የሚባለው ወሳኝ መሆኑን መረዳት አያዳግተንም ነበር፤ የተዳፈነውና □□ መቀ□ የሕዝብ የአካል፣ የአእምሮና የመንፈስ ኃይል ሊወጣ የሚችለው ሕዝቡ ነጻ ሲወጣና ስልጣንን ተረክቦ በራሱና በሕግ በመተማመን ለኑሮውና ለሕይወቱ ባለቤት የሚሆንበት ሁኔ□ ሲ□□ር ብቻ ነው:: በኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር፣ በኢትዮጵያ መምህራን ማኅበር፣ በኢትዮጵያ ነጻ ጋዜጠኞች ማኅበርና በከተማና በገጠር ቀበሌ ማኅበራት ላይ የሚደረገው አፈናና ጫና ዴሞክራሲን በኢትዮጵያ ለመገንባት አይረዳም:: ዴሞክራሲ የሚገነባው በልበ ሙሉ ዜጎች ነው፤ ማስፈራራትና ማስሸበር ቀርቶ የሥልጣን ትግል ሁሉ ሰላማዊና ሕጋዊ ሲሆን ነው:: በተፊ ማሪም □□ሞ□ራሲ ዓ ቅም እያንዳንዱ ዜጋ፣ ሕዝቡም በአጠቃላይ ለራሱ ኑሮና ለአገሩ እድገት ኃላፊነትን እንዲሸከም ማድረጉ ነው:: በአገዛዝ ሥር ያለ ሕዝብ ነጻነትም ኃላፊነትም □ለ□ም::

የኢትዮጵያን ህልውና ጠብቀን የሚቀጥለውን ትውልድ ከደህነት፣ ከችጋር፣ ከጦርነትና ከ□ርስበርስ እልቂት የሚያድነው የሕዝብ የሥልጣን ባለቤትነትና የሕግ የበላይነት በሚቀጥለው ምርጫ መ□ም□ሚጸ ጸ□ኛል ብለ□ □ሚጸምኑ ሰዎች ያሉ ይመስለኛል:: በምኞትም ሆነ በተስፋ ደረጃ ከእነሱ ፉር እቆማለሁ:: ግን ከፍተኛ ጥርጣሬ አለኝ:: የዛሬ አሥራ ሁለት ዓመት ግድም በየዋህነት አንድ ነገር ተናግሬ ነበር፤ ወያኔ ትክክለኛ ምርጫ አካሂዶ ከአሸነፈ ጥሩ፣ ካላሸነፈም ለኢትዮጵያ አዲስ የዴሞክራሲ ምዕራፍ ከፍቶ በክብር የሚቀጥለውን ምርጫ ይጠብቃል ብዬ ነበር፣ ይህ ምኞት ላም ባልዋለበት ኩበት ለቀማ ነበር:: በኋላ እንደተማርሁት እንኳን በዚያን ጊዜና ለምንጊዜም ሥልጣንን እንደማይለቅቁ ነው:: ሌላውን ሁሉ ትተን ለአገርና ለወገን የሚያስብ ሰው ከኤርትራ ጦርነት በኋላ ስሕተትንና ብዙ ጉዳዮችን ማስተካከል ይቻል ነበር፣ በድንበሩ ምክንያት የተነሣውንም ውዝግብ በአዲስ መንገድ መፍታት ሳይቻል አይቀርም ነበር::

በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ያንገዋበበውን አስከፊ ችግርና የአገሪቱንም ህልውና □ሚ□ታተነውን ሁኔታ □ጸቃለሉ መገመቱ በሁሉም በኩል ቁርጠኛነት እንዳይኖር ያደርጋል፣ እውነቱ አስደንጋጭ ቢመስልም ኮስተር ብለን እንድንዘጋጅ ይረዳናል:: የአእምሮና የመንፈስ ዝግጅትም ፅ□ታችን ይሆናል፤ አእምሮአችንንና ልባችንን ማፅዳትና መተማመን ያሻናል፤ ጠባችን የሀሳብ ልዩነት አይደለም፤ አለመተማመንና መፈራራት ነው:: መንገድ ፈልገን እንተማመን፤ እኛ በሰላም ተከባብረን ሀሳቦቻችን □ፉፉ ፣ □□ፉ ፣ በሚ□□□ም ብርሃን አገራችንን እንገንባ:: የአገራችን ጥሩ ባህል ስለነበረው እርቅ አለቃ አያሌው ታምሩ የሚከተለውን ጽፈዋል፤--

> *ወንድማማቾች በማይገባ ነገር ተ□ልተ□ በሃሳብ ተለጸ□ተ□፣ የማይግባቡና የማይሰማሙ ከዚያም አልፎ ነገራቸው ከዳኛ የሚያደርሳቸው አንዱ በአንዱ ላ□ □□ ለመሥራት የሚገፋፉቸው ሆኖ ሲገኝ ከፀቡ አግባብ የሌላቸው ወዳጆች፣ ጓደኞች፣ ባልንጀሮች፣ ሽማግሌዎች በመሐከል ገብተው ማል□□ በ□ቅር ተቆዓ ተ□ ወይም አባብለው ለዕርቅ ቢያደርሱአቸው ሊፈርስ የነበረ ቤት ይታነጻል፤ የፈሰሰ ደም ይደርቃል፤ ነባር ቂም በቀል □ርቃል::*[2]

መንፈሳዊ ወኔውን አግኝተን ይህን ለማድረግ ከቻልን ኢትዮጵያን ከአደጋ ማውጣት ብቻ ሳይሆን የምንከራባትና የምንመካባት አገር ልናደርጋት ችሎታው አለን፤ ከዱሮ ጀምሮ የነበረኝ እምነት ኢትዮጵያ ትክክለኛ መንግሥት ስታገኝ በአንድ ትውልድ የአፍሪካ ጃፓን ለመሆን ትችላለች ሆኖም ጊዜ የለንም፣ ዛሬ መጀመር አለብን::

---

[2] አለቃ አያሌው ታምሩ፣ ምልጃ፣ እርቅና ሰላም፣ አዲስ አበባ፣ 1992፤

# VISION 2020: WHITHER ETHIOPIA

**MESFIN WOLDEMARIAM**

**Translated by Yonas Admassu**

## I. INTRODUCTION

It may perhaps be necessary to understand the global situation in which we currently find ourselves. The horrible and barbaric attack of September 11, 2000 on America; America's comparable military response for that against Afghanistan and, then, against Iraq; its threats against North Korea, Syria, and Iran; and the actions of those that are called terrorists in Kenya, Indonesia, Iraq and Afghanistan have contributed to disturb the already fragile world peace. Perhaps, the principal cause of all this is the endless, and mindless strife between the Israelis and the Palestinians. On the one hand, while oppression that employs incomparably superior force is transforming Palestinian nationalism into Arab nationalism, and into Islamism, on the other hand, it is changing Israeli nationalism into Westernism or Americanism. As a consequence, the targets of the conflict are as varied as are the type of the weapons used. On the part of the Palestinians and their supporters, the target in this conflict is everyone on the side of America; everything considered as American property; everything considered as American interest. America and Israel, for their part, have as targets all those they call terrorists. The choice, however, both sides give to the rest of the world amounts to nothing more than: 'if you are not with me, you are against us.' The type of conflict is such as has never been heretofore witnessed in the world. The battlefield is borderless and practically covers the whole world. The type of weapons used is extremely varied. The weapons used by America and Israel are the products of modern technology, which, crush and burn effectively. The weapon employed by their adversaries is human life. Every week many lives are lost and much property destroyed on both sides. It is quite clear that on both sides evil spirit has prevailed over good.

The principles that enjoyed universal respect in the preceding century (Gregorian calendar) are now being violated. The sovereignty of states has now become something contingent upon the consent of the superpowers. We are all familiar with what happened in Yugoslavia, Afghanistan and Iraq in this regard. The threats directed to North Korea and Iran as well as against Syria by America and the consequent climate of uncertainty is an indication of superpower dominance. The American demand to replace an elected leader is now followed by Al Qa'ida. Looking at the state of affairs today, mass slaughter of human beings and the destruction of property and development infrastructures have become the standard practice and a matter of right not only for the powerful but also for the weak. Moral rectitude has reached the bottom in the realm of the spiritual, let alone in the secular sphere. The time is such that people are ready and willing to sell not only their bodies but also their souls. Human dignity and honor have no longer any value. This is how the world we live in today appears to me. And it is in such a world that we [Ethiopians] live in utter destitution and helplessness.

Although the general climate in the world we live in appears to be unfavourable to oppressive regimes, the superpowers, nevertheless, show a tendency to use oppressive regimes as instruments of their interest and policy. As far as terrorism is concerned the principal problem of the Western powers is their failure to comprehend that terrorism is a consequence of Western relations with oppressive regimes. As long as oppressive regimes continue to exist and peaceful political struggles are

suppressed, there will always be rebellion and terrorism. It is, consequently, inevitable that the target of rebellion and terrorism will be the destruction not only the oppressive regimes but also the powers behind them. I do not believe there is any other reason than this for America to be targeted as an enemy by terrorists. In spite of the fact that the American ideals of freedom, democracy, justice and property rights are of great benefit to all humanity, the American government has not demonstrated unshakeable faith in them and made them instruments of its foreign policy. On the contrary, the American government, for various reasons, becomes the supporter and defender of oppressive regimes. I think that is the problem.

The gap between the Western nations and the rest of the world is growing ever wider. The Western nations have achieved in a mere span of four hundred years what we have not been able to do in four thousand years. Because our planet has become too small for them, they are now moving further into the wide world of outer space. While we are still dragging ourselves behind our donkeys to cover a mere seven kilometers a day, they cruise comfortably through thousands of kilometers in a matter of hours. Whereas we fail to observe what is obvious and tangible, they persistently investigate and probe into the microscopic. While we purchase arms and weapons manufactured by the West to wreak havoc among ourselves, as if in celebration of death, they are relishing every bit of joy that life provides. While we have found it almost impossible to live peacefully together in the small space we have in our country, they are turning the whole world into their own country, whether we like it or not. We, for our part, hate the country that we have destroyed, and make a culture of going into exile in the West. For those of us who have not yet gone into exile, our lives, whether in the realm of the state or non-governmental organizations, are at the mercy of Western generosity. Our very survival has no security outside such generosity.

The question, therefore, for me is not what we have, but what we are.

## II. The Impact of the Global Situation on Our Life

The factors that pose challenges to the issue of Ethiopianness and its survival have their sources not only in the internal administrative setup, but also in external relations. History leaves behind its own scars. Various European colonial forces have been embarrassed by Ethiopia's impregnability; America, too, has experienced this impregnability; Turkey, Egypt and some Arab countries have seen, each in its own way, the impregnability of Ethiopianness. But it is an indubitable fact that there is an imprint, both biological and cultural, which history has left behind, shared by our neighbors and ourselves. And one such imprint [in the cultural-religious sphere] is Islam. Islam, as a religion, is as much Ethiopian as it is Arab. Before the advent both of Christianity and Islam in Ethiopia, Ethiopianness had a link with Bete Israel or Judaism. In my view, Judaism, Christianity and Islam had each attempted at various times to replace Ethiopianness; all failed. Instead, each became Ethiopian. To the same extent that Jerusalem became a sacred place of worship for all three religions, so also has Ethiopianness partaken of the history of this Holy place.

All three religions have adherents outside of Ethiopia. Because these religions have for long served as bridges between Ethiopia and other countries, mutual interactions among people, ideas and cultures have taken place, resulting in varying kinds and degrees of lasting relationships. Today, however, Ethiopian Judaism has shorn itself of its Ethiopian identity and has put on Israeli garb. Together with other forms of exile currently taking place, I think we can consider this particular exodus as the beginning of stripping of our sense of Ethiopianness of its potency.. On top of this, we are still in the dark as to what the impact of the Israelization of the Bete Israel would be on Muslim Ethiopianness. Christianity's Ethiopianness is in tatters as a result of commotion and strife generated by tribalism. It is only Islam that has courageously managed to resist the outrages of tribalism. It is possible that there are some who might try to involve Ethiopian Islam in the conflict the Western powers have with Islam, or, as it is generally referred to,

Islamic fundamentalism. Consequently, there is fear among some circles that Ethiopian Islam will, through some kind of external influence, indeed get involved in the conflict and contribute to the weakening of the sense of Ethiopianness and expose the country to danger. The regime's conflict with Somalia's Al Ittihad is rationalized on that basis. We should be careful not to let such conflicts poison the Ethiopianness of Islam. I have no doubt whatsoever that, at a time when the Ethiopianness of Christianity is being undermined by an inept internal administration, the additional weakening of the Ethiopianness of Islam as a result of external interference would certainly aggravate the erosion of Ethiopianness. While serving the interests of the Western powers lured by the power of their money may have its short-term advantages, the damage it inflicts on the country in the long term will have adverse consequences.

## III. Where Did We Start to Get Where We Are Now?

The regime of Atse Haile Selassie represented, for those of us who were young at the time, a system tangled up in an outdated cultural traits, a regime in which an unjust land tenure system prevailed, in short, a system that was backward and too slow to respond to the exigencies of the time. It may be unbecoming of me to reproach a regime that has now been dead thirty years. Yet, because it could not move along with the changing times and, moreover, could not even learn from and pay heed to the lessons of the 1960 attempt of a coup d'etat instigated and led by the Atse's own Body Guard, its downfall eventually proved to be unsightly and humiliating. The *Derg* regime that followed was, with all its baseness and ruthlessness, a child of the intransigence of the Atse's regime.

The achievements of the Atse's regime are quite substantial and cannot even be compared with those of the regimes that succeeded it. Let me briefly point out the major achievements of the regime in only three areas:

- First of all, regarding the issue of Ethiopian unity, we have come to learn of the efforts made to unite Eritrea with its motherland, thanks to a recent publication by Ambassador Zewde Retta; we have also learned from the same source that the current problems surrounding Ethio-Eritrean relations had their origin in that period;
- Secondly, leaving aside for the moment the land tenure system that prevailed at the time, it is my belief that Ethiopia, over and above being self-sufficient, would have been able to provide different agricultural products to the global market if only the progress started in agriculture had been allowed to continue;
- That the regime had taken Ethiopia to a point of self-sufficiency in the area of education is something that we are all familiar with.

I would like to deal with the issue of education at the time in more detail. Atse Haile Selassie habitually handpicked young people from wherever he went and had them enrolled in boarding schools. If such opportunity had not come our way, most of us could not even have been able to get anywhere near modern educational institutions, let alone get enrolled in any one of them. I remember, in Teferi Mekonnin School, for instance, there were Somalis from the Ogaden, Hararis from Harer, youngsters from Gojam, Gondar, Tigray, Sidamo, Arsi, Eritrea, Wellega and from around Addis Abeba itself enrolled as boarding students. Atse Haile Sillase was well aware of the legal concept in the *Fitiha Neghest: The son cannot be held accountable for the crimes of his father; neither can a father be held accountable because of his son's crime.* Accordingly, even the son of the infamous traitor, Haile Sillase Gugsa, and that of the rebellious patriot Belay Zelleqe were among those enrolled in the school at that time. When

this medley of students rebelled in the school, he angrily uttered “this is what happens after bringing them together from nothing!” Although what he said at the time was true as far as facts go, we felt hurt. And that is why a student, Matewos Tiggineh, retorted: "Your Majesty, our fathers, after all, pay their taxes!"

This traditional regime, however, had its controllers in the form of 'conscience' from within and God and fear of public opinion from without. There also was the pressure from the elderly. Moreover, not only Atse Haile Sillase, but also those in his service were sensitive about their honor. Accordingly, there were voices that they heard and listened to both from within themselves and from without. However, because dictatorial regimes cannot learn and correct themselves, the 1960 attempted coup failed to change it.

In my opinion, Atse Haile Sillase's regime has shown incomparably good progress by way of introducing and expanding modern education in Ethiopia. Education in general, and higher education in particular, were both open to any poor Ethiopian who was able to prove his/her worth. Children of the aristocracy and the nobility went to school alongside those of the poor. I still remember how, in 1951 Gregorian calendar, a report in *Life* magazine, stating that Ethiopia did not have even a single engineer, incensed me. The saving grace, however, came that same year when institutions of higher education were inaugurated. Without any doubt, the regime of the Atse had indeed launched Ethiopia into the twentieth century in the realm of modern education. This also was true in the military field. The military academy in Harer, the Ethiopian Air Force at Debre Zeit and the Naval Academy at Massawa provided all-round, high quality training. Ethiopia was even able to provide scholarships to young men from other African countries, some among which had become ministers and ambassadors of their respective countries.

ሌሎችም ምሳሌዎች መጥቀስ ይቻላል ግን ባጭሩ ፍሬ ነገሩ እስካሁን የታዩት መለስተኛ ጦርነቶች መንስኤቸው በአመዛኙ የጎሳ፣ የሀይማኖት፣ የቋንቋ ሳይሆን የተፈጥሮ ሀብት መመናመን፣ የኢኮኖሚና የኑሮ ጥያቄዎች ናቸው።

የዮሐንስ ራዕይ የሚያሳየን የኢትዮጵያ መጥፋት መቃረቡን ነው። እነዚህ አራት ፈረሰኞች በኢትዮጵያ ላይ ማንገዋበብ ከጀመሩ ብዙ ዓመታት አልፏል።

በመጨረሻ የማቀርበው ነጥብ ጎሰኝነትን ይመለከታል። እንደ ፕሮፌሰር መስፍን የጎሳ ፖለቲካ እኔንም አስጨንቆኛል፣ አሳስቦኛል። ይሁን እንጂ በእኔ ግምት የዚህች አገር መጥፊያ በአመዛኙ የጎሳ ፖለቲካ ሳይሆን ረሀብ፣ በሽታ፣ የተፈጥሮ ጥፋት፣ በአጭር አነጋገር የድህነት መስፋፋት ነው።

የማቀርበው ግንዛቤ እዚህ ላይ ያበቃል፥ ስላዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ!

# በፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም ጽሁፍ ላይ የተሰጡ አስተያየቶች

አሰፋ በቀለ
የአፍሪካ ህፃናት ፖሊሲ መድረክ

## መግቢያ

ዛሬ እፊታችን የቀረበው ጽሑፍ በጣም አስደንጋጭ ነው። ልናልፈው አንችልም። መልእክቱ ስለሚረብሽ ብቻ ሳይሆን፤ የተደረሰው በአንጋፋው ምሁር ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም በመሆኑም ነው!

ፕሮፌሰር መስፍን በርካታ ጠቃሚ ሥራዎችን የሠሩ፤ አያሌ ኢትዮጵያውያንን ያስተማሩ፣ ብዙ ጽሁፎችን ያበረከቱ፣ በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዩኒቨርሲቲ በኋላም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በነበሩበት ጊዜ ለአካዳሚክ ነፃነት የታገሉ፣ አሁንም እንደበፊቱ በፖለቲካው ዓለም ነፃ እና ብሄራዊ አቋም በመያዝ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ብዙ የታገሉ፣ ከአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ጀምሮ ጠቃሚና ዘላቂ ድርጅቶች በመገንባት ያገዙ፣ በተጨማሪም ወይም በተለይም የአገር ሁኔታን በማጥናትና በማስታወቅ እሮሮ እና እሪታ በማሰማት ይህ ነው የማይባል አስተዋጽኦ ያበረከቱ ታላቅ ኢትዮጵያዊ ናቸው።

ልናዳምጣቸውም ይገባል፤ እሳቸው ማሚረት ይወዳሉ፤ "…እስካሁን ድረስ ሦስት አገዛዞች በውርደት ሲወድቁ አይቻለሁ፤ የሁለቱ አገዛዞች መውደቅ በቅድሚያ ታውቆኝ በአደባባይ ተናግሬ ነበር። የአሁኑ አገዛዝ … ራሱን ለማረም በጊዜው ካልጣረ አወዳደቁም የተለየና አገሪቱንም የሚያጠፋ ሊሆን ይችላል…" ይሉናል።

## የትንተናው አቅጣጫ

ይህን ፅሁፍ ከብዙ አንፃር ለመተንተን ይቻላል። ከሱም ተነስቶ ብዙ ለመጻፍ በተቻለ፥ ግን ጊዜውም ቦታውም አይፈቅድልንም። በዚህም የተነሳ በሁለት ነገሮች ብቻ አተኩራለሁ። አንደኛ ይህ ጽሁፍ ምን አዲስ ነገር አዝሏል? ከዚያም ጋር አያይዤ ትችቶቹ በመረጃና በጥሩ ትንተና ተደግፈዋልን የሚለው ይሆናል። እነዚህንም ሁለት ጥያቄዎች ተከትዬ አከራካሪ መስለው የታዩኝን ለመጠቆም እሞክራለሁ።

## የጽሁፉ መለያ

ይህን ጽሁፍ ከብዙ ጽሁፎች (ከሞላ ጎደል) ለየት የሚያደርጉት አንዳንድ ነገሮች አሉ። በመጀመሪያ ይህ ጽሁፍ በአማረ ቋንቋ ብዙ ነገሮችን የዳሰሰ ነው። የምንገኝበትን የዓለምን ፖለቲካ፣ የአለፉትንና የአለውን የሶስት መንግሥታት ባህሪና ጉድለት፤ አሁን የምንገኝበትን ሁኔታ፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ ባህሪና አስተሳሰብ ወዘተ ይዳስሳል። የጽሁፉ ስፋት የድክመቱም አንዱ ምክንያት ነው ። ይህን ወደኋላ እመለስበታለሁ።

ይህን ጽሑፍ ለየት የሚያደርገው ሌላ ነገር አለ። አሁን በመካሄድ ላይ ያለው በአሜሪካን/በእስራኤልና በእስላሙ ዓለም (ወይም አክራሪ እስላሞች ወይም አሸባሪዎች በተቃዋሚዎቻቸው ቋንቋ) መሃከል እየተፋፋመ በመሄድ ላይ የአለው ግብግብ፣ በተጨማሪም በዚህ ጉዳይ ላይ የኢትዮጵያ መንግሥት የወሰደው አቋም በኢትዮጵያ ህልውና ላይ ሊያመጣው የሚችለው ችግር በይፋ ሲነሳ ለመጀመሪያ ጊዜ ይመስለኛል።

ሶስተኛ፣ ምንም እንኳ ቅድም እንደጠቀስሁት ለመጀመሪያ ጊዜም ባይሆን፤ ይህ ጽሑፍ የአለንበትን ወቅት ቁልጭ በአለ አስፈሪና አስደንጋጭ ቋንቋ ይገልፀዋል። "አሁን በተያዘው መንገድ መቀጠል አንችልም። የያዝነው መንገድ ወደክፉ ዕድል፣ ወደመዓት፣ ወደውድቀት፣ ወደ የጎሣ ትርምስና የቂም መወጫ… የያዝነው መንገድ ወደዚህ እንደሚያመራ ለእኔ ግልጽ ነው። ይህንን የሚጠራጠር ትንሽ ያስብበት…" ይላሉ መስፍን። "በጎሠኝነት ተኮትኩተው ያደጉ ልጆች እየደረሱ ነው፤ አንድ ትውልድ ሊሆን ምንም ያህል አልቀረውም። እኔ የማውቃትና አገሬ የምላት ኢትዮጵያ በከፊል የለችም፤ በያዝነው መንገድ ከቀጠልን ደግሞ ያሁንዋም ኢትዮጵያ በ2020 የምትደርስ አይመስለኝም፤ ከዘመነ መሳፍንት የባሰና አስከፊ ሁኔታ እንደሚያጋጥመንና በሆነ በአልሆነው መከሳከሳችን ይቀራል ብየ አልገምትም"። ይህን አነጋገር ልዩ የሚያደርገው፣ ብዙዎቻችን ስለአገራችን ሁኔታ ሊመጣ

ስለሚችለው ግጭት "እንሰጋለን" "እንፈራለን" ስንል እሳቸው ግን "ይሆናል" "አትጠራጠሩ" ይሉናል።

እንደገና ይባሱኑ፣ ፕሮፌሰር መስፍን "እኔ እንደምገምተው ሁሉም የተነበየው አዘቅት ወይም መዓት አፋፍ ላይ በ1997 መጨረሻ እንደርሳለን..." ይሉናል። ይህ አነጋገር ትልቅ ምርመራን፣ ወይም ባህታዊነትን ያለበለዚያም ትልቅ ድፍረትን ይጠይቃል።

እነዚህ ማስጠንቀቂያዎች የእብዱ መስፍን ቅዠቶች ናቸው ብለን እንዳናልፋቸው፣ አጻጻፉ፣ አወራረዱ፣ መነሻው መደምደሚያው የተደበላለቀ፣ የተዘበራረቀ አይደለም። የሃሳቦች አወራረድ፣ መነሻና አዘላለል ህብረት በአለው ትንተና የታቀፈ ነው። ይህንን ገጽታውን ከዳሰስሁ በኋላ አሁን ደግሞ አከራካሪ መስለው ወደታዩኝ ጉዳዮች ለማለፍ እወዳለሁ።

## ስለ ችግሩ

እንደእኔ አስታያየት ይህ ጽሁፍ አልፎ አልፎ ትንተናው ጥልቀት ያጣ ይመስለኛል። ይህም ያለምክንያት አይደለም። ታሪክን፤ ባህልን፤ ፖለቲካን በስፋት እንደዚህ የሚዳስስ ሁሉ ይህ ዓይነት አደጋ ያጋጥመዋል። ስፋትና ጥልቀት ብዙውን ጊዜ አብረው አይሄዱም። ለምሳሌ ያህል አንድ ጉዳይ ልጥቀስ።

የመስፍን ጽሁፍ መጋረጃውን የሚከፍተው፣ ሰፋ በአለ መንገዱ በአሜሪካኖች/ እስራኤሎችና በእስልምና ሐይማኖት ተከታዮች (ሽብርተኞች) መካከል የተፋፋመው ግጭት ለዓለም ፀጥታ ያስከተለውን ችግር በማንሳት ነው። ከዚያ ተከትሎ ይህ ግብግብ በኢትዮጵያውያን እስላሞች ላይ ወይም በሐይማኖቶች መሃከል ሊያስከትል የሚችለውን ችግር ጽሁፉ ነካ ያደርጋል። ከዚያ በኋላ ግን ጉዳዩ ሊነሳ ቀርቶ፣ ጭራሹንም ይረሳል። ይህ ደግሞ ያስገርማል። አንደኛ የድርሰቱ መነሻ በመሆኑ ነው። በድርሰት ዓለም ውስጥ በቅድሚያ የሚሰነዘረው ሃሳብ ወይም የሚታየው ተዋናይ ታሪኩን ወይም ትንተናውን ያሽከረክረዋል። ሌላው መረሳት የለበትም የምልበት ምክንያት አለ። የተነሳው የሐይማኖት ጥያቄ እጅግ አሳሳቢ፣ ከአልተጠነቀቅንበት ደግሞ በአጭር ጊዜ ውስጥ አንገብጋቢ ሊሆን የሚችል ጉዳይ ነው። ኢትዮጵያ በቁጥራቸው ተመጣጣኝ የሆኑ የክርስትናና የእስልምና አማኞች አገር ነች። በውጭ ተጽዕኖ ወይንም በውስጥ የፖሊሲ ስህተት በሁለቱ ታላቅ ሃይማኖቶች ችግር ቢፈጠር የሚከተለው ጣጣ ከጎሳው ግጭት የከፋ ይሆናል። በአዟሪትም የጎሳ ግጭቱን ሊያከረው ይችላል። ስለዚህም የጥናት ድርጅቶች የሐይማኖትን ጉዳይ ትኩረት ሊሰጡት ይገባል። ብዙ ጥያቄዎች ሊነሱና ሊመረመሩ የሚገባ ይመስለኛል። እስላም ወገኖቻችን ስለአገራቸው፤ ስለፖለቲካው፤ ስለአለንበት ምን ያስባሉ? ምኞታቸው ወይም ቅሬታቸው ምን ይመስላል? አገራችን እስልምናዋንና የምትገኝበት የጥገኝነት ፖለቲካ የሚያመጣባትን ተጽእኖ እንዴት ልታገናዝባቸው ትችላለች? እነዚህና ተመሳሳይ ጥያቄዎች በቅድሚያ፤ ሳይውል ሳያድር ቢጠኑ መልካም ይመስለኛል።

ሁለተኛ ጽሑፉን አከራካሪ የሚያደርገው የትንቢታቸው ቀጥተኛነትና እርግጠኝነት ነው። ብዙ ትንተና ከአደረጉ በኋላ ወደ ጽሁፋቸው መጨረሻ እንዲህ ይላሉ "እኔ እንደምገምተው ሁሉም የተነበየው አዘቅት ወይም መዓት አፋፍ ላይ በ1997 መጨረሻ እንደርሳለን" ይሉናል። "እሰጋለሁ"፤ "እፈራለሁ" ማለት አንድ ነገር ነው። በእርግጥ "ይሆናል" ማለት ግን የተለየ ነገር ነው። ይባስም በ1997 መጨረሻ አገሪቷ ትወድማለች ማለት ደግሞ የበለጠውን አስገራሚም አስደናቂም ነው። በጽሁፋቸው ውስጥ ፕሮፌሰር መስፍን በምን ጥናት ወይም ምርምር ላይ ተመርኩዘው ይህን ለማለት እንደበቁ ግን አይነግሩንም።

ሌላው አከራካሪ መስሎ የታየኝ፣ ጽሑፉ ስለኢትዮጵያ ህዝብ ባህሪ የሚያንጸባርቀው የተቃረነ አስተያየትና ትንተና ነው። እንደ ኢትዮጵያ ሕዝብ ብዙ የተተቸበት፤ በሌላ በኩል ደግሞ እንደ ኢትዮጵያ ሕዝብ ብዙ ያልተጠና የአለ አይመስለኝም። የተማረውም የአልተማረውም እንደአመቸው፤ እንደሁኔታው ይተቸዋል። ፕሮፌሰር መስፍንም ከዚህ ፈታኝ ዝንባሌ አላመለጡም። አንዴ "የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላማዊና መከራን የሚችል ነው፤ እንደኛ ደግና ትዕግስተኛ ሕዝብ የለም"፤... ይሉታል። ብዙ ፈቀቅ ሳይሉ ራሱን ወዳድ፤ "ለማሰብ ዝንባሌውም ፍላጎቱም" የሌለው፤ "ያለው ላይቀር ምን አታገለኝ" እያለ የሚኖር ይሉታል። ይቀጥሉና "ልባችን በክፋትና በጥላቻ፤ በቂምና በምቀኝነት የተሞላ ስለሆነ የልባችንን የሚያውቅ አምላክ የአፋችንን ፀሎት የሚሰማበት ጆሮ ያለው አይመስለኝም" ይሉናል። አሁንም ይቀጥሉና "ጎመን በጤና በሚል ሰንካላ ፍልስፍና የምንኖር፤ መንፈሰ ደካማዎች" ነን ይሉናል። እነዚህን የሚመስሉ ከባድ ቃላቶችንና

አስተያየቶችን ይሰነዝራሉ። ምንድነው የሚሉን ፕሮፌሰር መስፍን? የኢትዮጵያ ሕዝብ የትኛው ነው? ደጉ ነው ወይስ ምቀኛውና ክፉው። ጀግናው ነው ወይስ ፈሪው?

በራሴ አስተሳሰብ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከሌላ ሕዝብ የተለየ አይደለም። በሰውነቱ በመሠረቱ፤ እንደሌላው ሕዝብ ደግ ነው፤ እንደሌላው ራሱን ይወዳል፤ እንደሌላው ቸርም፣ ሌባም፣ ፈሪም፣ ጀግናም ነው። ከሌሎች የሚለየው የአለበት የዕድገት ደረጃና የሚኖርበት አካባቢ የሚያቀርብለት እንቅፋት ወይም የዕድል ውሱንነት ነው። የኢትዮጵያን ሕዝብ ከማኩሰስ ወይም አጋኖ ሰማይ ላይ ከማውጣት ይልቅ፤ በሱ ላይ የተደነቀሩትን ማነቆዎችና እንቅፋቶች ምን እንደሆኑና እነሱም በሱ ላይ ምን ዓይነት ተጽዕኖ እንደአደረሱበት ማጥናቱ የተሻለ ይመስለኛል። እንደገና በዚህም በኩል እንደ Forum For Social Studies ያሉት የጥናት ድርጅቶች ስለ ሕዝቡ ሥነ ልቡና፤ ስለፍርሃቱ፤ ስለጭንቀቱ፤ ስለፍላጎቱ፣ አንዱ ክፍል ከሌላው ይለይ ወይም አይለይ እንደሆነ፣ እንዚንና እንዚን የመሰሉ ጥናቶችን ቢያደርጉ ብዙ ይጠቅመናል። በምንወያይበት ጊዜ ነገሮችን ለመገንዘብ፤ የአስተያየት ልዩነትንም ለማጥበብ ያግዙናል።

እንደዚህም ዓይነቶች መረጃዎች ስለሌሉን (ወይንም ተረትና ስሜታዊነት ስለሚያጠቃን) ነው ፕሮፌሰር መስፍን ለኢትዮጵያ ሕዝብ በክፉም በደግም የተጋነነ የባህሪ ገጽታዎች እንዲሰጡት ያደረጋቸው። ለዚህም ነው ለምሣሌ ወደሌላ አከራካሪ ትችት የገቡት። በጽሑፋቸው የኤርትራን ጉዳይ አንተርሰው "ለሞት በቀላሉ እንነዳለን፤ ለሕይወት ግን በሰላም ለመታገል እንፈራለን… ለጦርነት የምናሳየውን የጋለ ስሜት ለሰላማዊ ትግል አናሳይም፤" ይሉናል። እርሳቸውን ደነቃቸው እንጂ፤ እርሳቸው እኮ ጨርሰውታል! "ማሰብ በጡንቻ እየተጨፈለቀ፤ ሰው እንደ እባብ ራሱን እየተቀጠቀጠ ነው" ብለዋል። ሁናቴው እንዲህ ነው ከተባለ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ መኮነን ተገቢ ነውን? ዘመቻ አልሄድም ቢል (የርሳቸውን ቃል ልጠቀምና) ይቀጠቀጣል። ሰላማዊ ሰልፍ ልውጣ ቢል ይቀጠቀጣል። ባይቀጠቀጥም በግራም በቀኝ ዋጋውን ይከፍላል። ይህም ማለት የኢትዮጵያን ሕዝብ በክፉም በደግም ከማንሳታችን በፊት የሚገኝበትን ሁኔታ ማጤን ያስፈልጋል።

## ስለ መፍትሔው

በአጠቃላይ ለችግራችን መፍትሔው፣ የህግ የበላይነትና ዲሞክራሲ መስፈን መሆኑን መስፍን ያሰምራሉ። መልካም ሃሳብ፤ ምኞትና ዓላማ ይሁን እንጂ፤ ለውይይታችን ግን አጥጋቢ መደምደምያ አይመስለኝም። እኔን እንደሚታየኝ፤ ውይይቱ ፍሬያማ እንዲሆን ከተፈለገ፣ የሕግ የበላይነትንና የዲሞክራሲን አስፈላጊነት ከማውጋት አልፈን መሄድ ያለብን ይመስለኛል። የድሮውም የአሁኑም የፖለቲካ አስተያየት ወይም ብስለት - ይቅርታ ይደረግልኝና - በአገራችን የቀጨጨ ነው የሚል ስጋት አለኝ። ተማሪዎች ሆነን በኋላም ድርግና የእኛ ጓደኞች ሥልጣን ሲወስዱ፤ ዝም ብለን የስታሊንን ፍልስፍና እንደ ደብተራ ስንደግም ኖርን። ዕውቀት በካርል ማርክስ ተጀመረ፤ በሌኒንና በስታሊን ተደመደመ። አሁንም ቢሆን ዲሞክራሲ ዲሞክራሲ ብለን ቀጥ እንላለን። ብዙ ጥያቄዎችን ልናነሳ እና ልናጤናቸው ያስፈልጋል። አሁን በምንገኝበት ሁናቴ የዲሞክራሲያዊ ኃይሎችን ለማጠናከር፣ ዲሞክራሲን ለማንገስ የሚያስችለን ስትራተጂ ምን ይመስላል? ዲሞክራሲ ስንል ምን ማለታችን ነው? የጎሣና የሐይማኖት ጥላቻን እንዳያባብሰው ምን ዓይነት ዝግጅት ወይም ጥንቃቄ ብናደርግ ይበጃል? ለአገር አንድነት በአንድ በኩል በሌላ በኩል ደግሞ የጎሣዎችን ፍላጎት ለማሟላት የሚያስችለን ምን ዓይነት የመንግሥት አቋም ይበጃል? አሁን ያለው የፌደራል ተቋም ወይስ ሌላ? ሌላስ ተሆነ ምን ዓይነት? እኒህን የመሳሰሉ ጥያቄዎችን አንመለከታቸውም። ግን ውይይታችን እርባና እንዲኖረው ከተፈለገ ከመፈክር ማለፍ አለብን።

በመጨረሻ ከነዚህ ጋር አያይዤ ሁለት ነገሮች ለማከል እፈልጋለሁ። መስፍን ወደ ጽሑፋቸው መደምደሚያ ላይ "ጠባችን የሀሳብ ልዩነት አይደለም፤ አለመተማመንና መፈራራት ነው"። ከሞላ ጎደል ትክክል። እንዲያውም ቁልጭ አድርገው "… መሣሪያ የያዘውም ይፈራል፤ መሣሪያ ያልያዘውም ይፈራል … የሁለቱም ጠላት አለመተማመንና መሣሪያ ነው። አለመተማመንን ሳናጠፋ መሣሪያውን ማጥፋት አንችልም፤ ሳንነጋገር አለመተማመንን ማጥፋት አንችልም…" ይላሉ። ትክክል። ጥያቄው እንዴት ነው እምንተማመነው? እንዴት ነው የምንነጋገረው? ነው።

በራሴ አስተሳሰብ በልዩ ልዩ ወገኖች በተለይም በመንግሥትና በተቃዋሚ ክፍሎች (ምሁራንን ጨምሮ) የአለው ግንኙነት (ወይም ኩርፊያ) ጤናማ አይመስለኝም። በሁሉም በኩል የማንኳሰስና

የማክረር ባህሪ ይታያል። የመንግሥት ደጋፊዎችና ካድሬዎች - በተለይም ከጦርነቱ በፊት - ስለኢትዮጵያ አንድነትና ሉአላዊነት በሚወራበት ጊዜ ይህ "ነፍጠኛ" እያሉ፤ ሲያበሻቅጡ ነበር። ጠቅላይ ሚኒስትሩም መሠረታዊ ጉዳዮች ሲነሱ "ይህ የሞተለት ጉዳይ ነው፤ መንገዱን ጨርቅ ያርግልህ፤" እያሉ ቁምነገሮችን ያጣጥላሉ። የፖለቲካ ኑሮ ድርድርን እንደሚጠይቅ ባለመገንዘባችን "ከአልጨፈለቅሁ እጨፈለቃለሁ" በሚል ፍርሃት ልዩነቶች ይከራሉ፤ ልዩነት የሚፈታውም በእስር ቤት ወይም በግድያ ይሆናል። በአኳያው በምሁሩ በኩልም፣ መንግሥትን በጭፍኑ የመኮነን ባህሪ ይታያል። ይህ ትክክል አይመስለኝም። ዓለም፤ ሙሉ በሙሉ ጥቁር ወይም ነጭ አይደለችም። መወያየት መቻቻል አስፈላጊ ይመስለኛል። እናክርር፤ ቋንቋችንን እንቆጥብ፤ እንቻቻል፤ እንወያይ። ይህን ካላደረግን፤ ከአሁኑ የባሰ ሥርዓት ውስጥ እንወድቃለን ብዬ እሰጋለሁ።

ሌላም ተጨማሪ ነገር አለ። የኢትዮጵያ ችግር በቀላሉ የሚፈታ አይደለም። ፈጣን ወሳኝ ለውጥ መፈለግ የት እንዳደረሰን እናውቃለን። ትግሉ ረጅም መሆኑን መገንዘብ ያለብን ይመስለኛል። ይህም ማለት፣ አንደኛ ሕዝብን ማስተማር፣ ማሳወቅ፣ እንዲደራጅ ማድረግ ነው። ሁለተኛው ሕዝብ እንዲተዋወቅ፣ እንዲቀራረብ ማድረግ ነው። አሁን ያለው እሰጥ አገባ በመንግሥትና በተቃዋሚ ኃይሎች ወይም ምሁሮች መሃከል ነው። ሕዝብና ሕዝብን ማወያየት አስፈላጊ ይመስለኛል። የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ማህበር ያዘጋጀው ይህ መድረክ ለዚህ ዓላማ ጠቃሚ ነው። ይበረታታ፤ ሌሎችም ይህን ምሣሌ እንዲከተሉ እንመኛለን።

## መደምደሚያ

እንደ ፕሮፌሰር መስፍን እኔንም አሁን ያለንበት የኢትዮጵያ ሁኔታ በጣም ያሳስበኛል። እንደእሳቸው የኢትዮጵያ መንግሥት በመካከለኛው ምሥራቅ የወሰደው እርምጃ የአገራችንን ሰላም ሊያደፈርሰው ይችላል የሚል ስጋት አለብኝ። እንደእሳቸው የኢትዮጵያ አንድነትና የህዝቧ ህብረት ክቡር ነው፤ ይህም ይናጋል ብዬ እሰጋለሁ። እንደእሳቸው ሃይማኖትንና ጎሳን ከፖለቲካ ጋር ማቆራኘት በእሳት ላይ ቤንዚን እንደመርጨት አድርጌ እቆጥረዋለሁ። ስለዚህ እንደ እሳቸው እኔንም የሐይማኖትና የጎሳ ጦርነት ያስፈራኛል። በአጠቃላይ እምነታቸው እምነቴ፤ ሥጋታቸው ሥጋቴ ነው። ሆኖም ወደ መፍትሔው ስንመጣ ግን ከመፈክር ደረጃ ያለፍን አልመሰለኝም። በፖለቲካ ምርምር፣ ጥናት፣ ጥልቀት ገና ገና ብዙ የሚቀረን ይመስለኛል። ስለዚህም የምሁሩ ዋና ተግባርና ሚና፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ ባህሪ፣ አስተያየት፣ ችግርና ፍላጎት ማጥናት፣ ማስተማር፣ ማስታወቅ፣ ፍላጎቱም በተግባር የሚተረጎምበትን ዘዴና ስትራተጂ ማውጣት ነው። ይህን ከተቀበልን ፕሮፌሰር መስፍን ያቀረቡልን ድፍረትና፤ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር የቆሰቆሰው ጫጫታ ትልቅ የቤት ሥራ ጥሎብናል እላለሁ። ውይይቱ ጀመረ እንጂ አላለቀም። ስለዚህ ውይይቱ ይቀጥላል።

**Please visit our new web address for updates at the EEA/EEPRI**

**http://www.eeaecon.org**

# ከአገር ውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በአገር እድገት የሚኖራቸው ሚና

ብርሃኑ ነጋ

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ምርምር ተቋም

*ይህ ፅሁፍ በዶ/ር ብርሃኑ ነጋ በአመስተርዳም ለኢትዮጵያውያን ማህበረሰብ የተደረገ ንግግር ነው፡፡ እዚህ እትም ላይ የወጣው ስለ ስደት የሚጠቅሰው ክፍል ነው፡፡ ቀሪው ክፍል ርዕይ 2020ን የተመለከተ ስለሆነ፣ በልሳነ ኢኮኖሚክስ Vol. 5 No. 4፣ July 2003 ላይ ያገኙታል፡፡*

## መፅቢጸ

በመጀመሪያ አገራችን አሁን ባለችበት ሁኔታና ከፊቷ በተደቀኑት ችግሮች ላይና እነኝህን ችግሮች ለመቅረፍ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የሚኖራቸውን አስተዋፅኦ በሚመለከት ያለኝን አስተያየት እንዳቀርብ በአምስተርዳም የኢትዮጵያውያን ማህበር ስለጋበዘኝ በጣም አመሰግናለሁ፡፡

## ስለ ስደት አጠቃላይ

ምንም እንኳን በዓቅሉ ሲ□□ አንድ ሰው በህይወት ዘመኑ የበለጠ □ስተኛ ሆኖ ለመኖር ተወልዶ ባደገበት፣ ሕዝቡን፣ ባህሉን፣ አኗኗሩን፣ አመጋገቡን በለመደበት እና በሚያውቅበት፣ በዚህም ምክንያት የባለቤትነት ስሜት (sense of belonging) የሚሰማበት አገር እንደሆነ ቢታመንም በተለያየ ምክንያት በትውልድ አገራቸው ያለው ሁኔታ ያልተመቻቸው /ለምሳሌ በፖለቲካ ምክንያት ግን በአብዛኛው በኢኮኖሚ ነክ ጉዳዮች/ ወይንም ደግሞ ለተወሰነ ጊዜ ያሉበትን የኑሮ ሁኔ□ ለማሻሻል/ በትምህርት ወይንም በሥራ/ አገራቸውን ለቀው የተሰደዱ ሰዎች መኖራቸው የቆየና የተለመደ የሰው ልጆች ድርጊት ነው፡፡ በ□ሪ□ እንደ አሜሪካና አውስትራሊያ ያሉ አገሮች የተመሰረቱትም /ቢያንስ አሁን በሚታወቁበት አይነት/ ከተለያዩ አገራት በፈለሱ በእንዲህ አይነት ስደተኞች ነው፡፡

የሰዎች አገራቸውን ለቀው መሰ□□ ምክንያቱ እንደ አገሩ ሁኔታና እንደጊዜው ይለያያል፡፡ በአገሮች □ስዓ □ሚ□□ር □□ለቲካ አለመረጋጋትና ነውጥ የስደት አንደኛው መነሾ መሆኑ □ታወቃል፡፡ የ1947 የቻይና አብዮት፣ የ1966ቱ የኢትዮጵያ አብዮትና እሱን ተከትሎ የመጣው ያላቋረጠ የፖለቲካ አለመረጋጋት ለብዙ ህዝብ አገሩን ለቆ መሄድ ወይንም ቀድሞ በሌላ ምክንያት ለአጭር ጊዜ ብሎ ለሄደው ላለመመለስ ምክንያቶች መሆናቸው ግልፅ ነው፡፡ በአህጉራችን በአፍሪካ እንደ ሱዳን፣ ኮንጐ ዴሞክራሲጸዊ ሪፑብሊክ፣ ላይቤሪያና ሶማሊያ □መሳሰሉ □እርስ በርስ ግጭቶች ለብዙ የየአገራቸው ህዝቦች ወደ ጐረቤት አገሮች መሰደድ ምክንያት ሆነዋል፡፡ የስደት አንድ አይነተኛ ባህሪው ደግሞ ለስደቱ መነሻ የሆነው ምክንያት /በተለይ የፖለቲካና የሲቪል ግጭት/ መፍትሄ ሲያገኝ የተሰደዱት በሙሉ ወደ አገራቸው ይመለሳሉ ማለት አይደለም፡፡ በተለያ□ ምክንያት/ የስደትን ኑሮ በመልመድም ጭምር/ የስደት ምንጩ ሲደርቅም በወጡበት □ሚቀሩ ሰዎች ቁጥራቸው ትንሽ አይደለም፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ስደቱ የተፈጠረበት ምክንያት ቢፈ□ም የመፍትሄው አይነትና ይዘት ስላልጣማቸው ሊሆን ይችላል፡፡ /ለምሳሌ ሩዋንዳ፣ ኢትዮጵያ/ መፍትሄውን በአይነቱም በይዘቱም ወደውትም ቢሆን ከመፍትሄው በኋላ በስደት ከለመዱት የኑሮ ሁኔታ ጋር አዲሱን የአገራቸውን ሁኔ□ በማ□□□ር /ሁኔ□□ □ስኪሻሻል/ መሰደድን በመምረጣቸው ይሆናል /ኤርትራ/ ወይም ደግሞ የስደትን ኑሮ በመልመድ አዲሱን ኑሮአቸውን ኑሮ ብለው በመያዝ ሊሆን ይችላል፡፡ ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን ግን የስደት ምክንያት አንዴ ከተፈጠረ በኋላ ችግሩን ጊዜያዊ ብቻ ነው ብሎ ለማለት ጸ□ፅ□ል፡፡

ከፖለቲካ ነውጥ ውጪ ምናልባትም በስደት □ሪ□ ቅ□ሚጸ የያዘው ከአገር የተሻለ የተመቻቸ የኢኮኖሚ ኑሮ በመፈለግ የሚደረግ ስደት ነው፡፡ በተለይ አዲስ የኢኮኖሚ እድል በአንድ ሁኔታ ሲፈጠር ከዚህ □□ል ለመ□ቀም ከአገራቸው ካላቸው የኑሮ ሁኔ□ ጋር በመመዘን ይህን አዲስ □□ል በመጠቀም ኑሮአቸውን ለመደጐም የሚሹ ብዙ ሰዎች አገራቸውን ለቀው ይሄዳሉ፡፡ ከላይ እንደጠቀስኩት በዚህ አይነት □ተ□□ሩ አዳዲስ አገሮች በ□ሪ□ ታይተዋል፡፡ በመካከለኛ□ ምስራቅ የዘይት ሀብት በተገኘበት ጊዜ ከብዙ እስያና አፍሪካ አገሮች ወደዚህ □□ለ አለም የተደረገ ስደት በአሁኑ ጊዜ ደግሞ ከብዙ የአፍሪካ አገሮች /ኢትዮጵያን ጨምሮ/ የተሻለ ኑሮ ለማፅኘት ወደ የትኛውም የአለም □□ል ለመሰ□□ □ሚ□ረ□□ ሩ□ የዚህ አይነቱ ስደት አይነተኛ ባህሪ ነው፡፡

በምንም ምክንያት ይሁን አገራቸውን ትተው የተሰደዱ ሰዎች ከትውልድ አገራቸው ጋር ያላቸው ትስስር/ ዜግነታቸውን ከቀየሩ በኋላ እንኳን/ እንዲህ በቀላሉ የሚቆረጥ አይደለም:: ሁሉም ማለት ይቻላል ይብዛም ይነስም በአዲሱ አገራቸው የድሮ አገራቸውን ማህበረሰብ (community) □□ዓ ራሉ፣ እንዳንዶቹ እንዲያውም በሥራ ጉዳይ ከሚኖራቸው ግንኙነት □·□ ሌላ□· ህ□□ታቸው በሙሉ ከአዲሱ አገር ህዝብ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም:: የተወሰኑት ከትውልድ አገራቸው ጋር የቅርብ ግንኙነት አላቸው:: ፖለቲካውን ይከታተላሉ፣ በአገር ውስጥ ካሉ ሰዎች ጋር በቅርብ ይገናኛሉ፣ በአዲሱ አገራቸው ሆነው በትውልድ አገራቸው ፖለቲካና ማህበራዊ ህይወት ውስጥ በጥልቀት ይሳተፋሉ:: ለተቸገሩ ዘመዶቻቸው ገንዘብ ይልካሉ፣ ለራሳቸውም ለወደፊቱ አገራቸው ሲመለሱ የሚኖራቸውን ኑሮ ለማመቻቸት የመኖሪያ ቤት □ሰራሉ፤ አልፎ አልፎም የንግድ ተቋማት ይፈጥራሉ:: በአንዳንድ አገሮች በውጭ ከሚኖሩ ዜጐች □ሚ□ኘው የውጭ ምንዛሬ የትውልድ አገራቸው ወደ □·□ ምርት በመሸጥ ከም□□ኘ□· □ቢ አይተናነስም አንዳንዴም ይልቃል::

**ሠንጠረዥ 1:** በተወሰኑ አገሮች በወጭ ከሚኖሩ ዜጐች የሚላክ የገንዘብ መጠን (ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር)

| 1998 እ.ኤ.አ | ኢትዮጵያ | ፅብ□ | ሞሮኮ | ሜ□ሲኮ | ዮርዳኖስ |
|---|---|---|---|---|---|
| አጠቃላይ ገንዘብ በዶላር | 293.4 | 3,262 | 1,998 | 5,627 | 1335.6 |
| % ከአጠቃላይ አመታዊ ምርት | 4.91 | 3.95 | 5.55 | 1.34 | 51.6 |
| በነ□ስ ወከፍ የሚደርሰው | 4.89 | 53.2 | 71.6 | 58.22 | 212 |
| **1999 እ.ኤ.አ** | | | | | |
| አጠቃላይ ገንዘብ በዶላር | 275.1 | 3.195 | 1.918 | 59.09 | 1317.8 |
| % ከአጠቃላይ አመታዊ ምርት | 4.58 | 3.6 | 5.43 | 1.23 | 32.5 |
| በነ□ስ ወከፍ የሚደርሰው | 4.46 | 5.1 | 67.9 | 60.22 | 203.4 |
| **2000 እ.ኤ.አ** | | | | | |
| አጠቃላይ ገንዘብ በ□ላር | 374.4 | 2,817 | 2,138 | 6,572 | 1486.3 |
| % ከአመታዊ ምርት | 5.58 | 3.1 | 5.91 | 1.13 | 35.44 |
| በነ□ስ ወከፍ የሚደርሰው | 5.9 | 44 | 74.5 | 65.56 | 223.2 |

ከላይ በሰንጠረዥ 1 እንደሚታየው ከነኝህ ለናሙና ከቀረቡ አገሮች በ□·ጭ ከሚኖሩ ዜጐቻቸው ወደ አገር የሚላከው ገንዘብ እንዲህ በቀላሉ □ሚታይ አይደለም:: ከተጠቀሱት አገሮች ውስጥ በገንዘብ መጠን ወደ ሜክሲኮና ግብፅ የሚላከው ከፍተኛውን ደረጃ የያዘ ሲሆን የሜክሲኮ በአማካይ በየአመቱ እየጨመረ መጥቶ በ2000 □ም ከ6.5 ቢሊዮን ዶላር በላይ የደረሰ ሲሆን የግብፅ ደግሞ እየቀነሰ ከ1998 3.2 ቢሊዮን የነበረው ወደ 2.8 ቢሊዮን ወርዷል:: የሚላከው ገንዘብ በአገሪቱ ላለው ህዝብ በአኩል ቢካፈል እያንዳንዱ ዜጋ ምን ያህል ይደርሰዋል በሚለው እሳቤ ከፍተኛውን ቦታ የምትይዘው ዮርዳኖስ ስትሆን በ2000 □ም እያንዳንዱ ዮርዳኖሳዊ ከውጭ ከሚላከው ገንዘብ 223 ዶላር □□ርሰ□ል፤ ይህም ከአገሩ አመ□ዊ የነ□ስ ወከፍ ገቢ □ሩቡን ይሆናል:: በዜጐች ከውጭ የሚላከው ገንዘብ ምንም እንኳን እያደር □□ሯ መረ ቢሆንም በመጠኑም፣ በነ□ስ ወከፍ □□□ሉም □ፀ ፅ □ቅተኛ የሆነው የኢትዮጵያ ሲሆን በጣም ትልቅ በነበረበት በ2000 ዓ.ም አጠቃላይ መጠኑ 374 ሚሊዮን፣ የነ□ስ ወከፍ ድርሻው ደግሞ ወደ 6 ዶላር ብቻ ነው:: ይህም ሆኖ ግን በኢትዮጵያ እንኳን ይህ መጠን አገሪቱ ወደውጭ □ቃ በመላ□ ከም□□ኘው ከግማሽ በላይ ነው:: በአጠቃላይ ይህ የሚያሳየው በውጭ የሚኖሩ □□ች ለትውልድ አገራቸው የኢኮኖሚ ገፅ□ ላ□ የሚኖራቸው ሚና ቀላል እንዳልሆነ ነው:: በዚህም ምክንያት በትውልድ አገር የሚገኙ የመንግሥት ባለሚሎች ይህን ሀብት ይንከባከባሉ::

ሌሎች ደግሞ ቁሳዊ በሆነ መልኩ ይህ ነው የሚባል ትስስር ባ□□ዓ ሩም የትውልድ አገራቸውን በትዝታቸው ይዘው አቅም በሚፈቅድላቸው ጊዜ ወይንም የተለየ አጋጣሚ ሲፈጠር ወደ ትውልድ አገራቸው ለአጭር ጊዜም ቢሆን ተመልሰው ትዝታቸውን ያድሳሉ:: ይህንንም ሲያደርጉ ለአገራቸው የውጭ ምንዛሪ ያስገኛሉ::

የሰዎች ከአገራቸው መፍለስ በአገራቸው ላይ የሚፈጥረው እንድምታም እንደ አገሩና እንደ ሁኔታው ይለያያል:: አንዳንድ አገሮች የህዝባቸውን መፍለስ ከሚሰጠው ኢኮኖሚያዊ □ቀሜታው አንፃር በመመልከት

ሥር□ት ባለው መንገድ አደራጅተው ያስኬዱ□ል:: ለሌሎች □ፅሞ □ህ□ብ መ□ለስ በተለ□ የኑሮ ሁኔታው ከተሻሻለው አካባቢ (ከተማረው ክፍል ለምሳሌ) በሚሆንበት ጊዜ አገሪቱ እድገት ላይ የሚያመጣውን ችግር በመመልከት ስደቱን ለመግታት ይጥራሉ:: በአጠቃላይ ስደት እንደ አገሩ ሁኔታ፣ እንደ ጊዜውና እንደሚመለከተው የህብረተሰብ ክፍል ለአንድ አገር እድገት አጋዥም እንቅ□ት ፈጣሪም ሊሆን ይችላል:: ስለዚህም ነው ስለ ስደትና እድገት ስናወራ ጥቅምና ጉዳቱን በጥቅሉ ከማውራታችን በፊት የአገሩን ሁኔታ ጠለቅ ብለን መመልከት የሚኖርብን::

በኢትዮጵያ ስደት (በተለይ እንዲህ በተጠናከረ መልኩ) የአጭር ጊዜ ታሪክ ነው ያለው:: አገርን ለቆ መሄ□ እንደ ነውርና ሀፍረት በሚቆጠርበት ጊዜ አገር ውስጥ መኖር እንደ ጅልነት እስከሚቆጠርበት ጊዜ (በተለይ በወጣቶች) ያለፉት ከሶስት አሥርት አመታት □ምብ□ም አያልፍም:: ምንም እንኳን በተለይ በሥራ ፍለጋ ምክንያትና በትምህርት ፍለጋ በቅድመ አብዮት ዘመን መጠነኛ ቁጥር ያላቸው ኢትዮጵያውያን በውጭ አገር ቢኖሩም በተለይ በፖለቲካ ምክንያት (ይህም ፖለቲካው የፈጠረውን ሽብር በመሸሽ የወጣውን ይጨምራል) አገር ጥሎ መሄድ በሰ□□ □ተጀመረው በደርግ ዘመን መሆኑ ብዙ አያከራክርም:: ይህ በደርግ ዘመን በሰፊው የተጀመረ □□ለቲካ ስደት ግን እራሱን ከሌላው ደብቆ ይኖር የነበረውን የኢትዮጵያን ህዝብ ከሌላው አለም ጋር በሰፊው አስተዋውቆ□ል ማለት ይቻላል:: ልጆቹን ከደርግ በትርና ብሄራዊ ውትድርና ለማሸሽ «የቻለው በቦሌ ያልቻለው በባሌ» መንቀሳቀስ የጀመረው በተለይ የአገሪቱ ልሂቅ ስደትን ቀስ በቀስ እየተላመደውና እየወደደው ሄዶ በውጭ አገር የተሰደዱ ልጆች ብዛት (በዚያ አገር ምንም ይሰሩ ምን) ቀስ በቀስ ለቤተሰብ □መፈሪጸ ተቀማጭ ሂሳብ አልፎም የስኬት መለኪያና መኩራሪያ መሆን ከጀመሩ ሰንበትበት ብሏል:: የፖለቲካ ሁኔታው ትንሽ ከተረጋጋም በኋላ ቢሆን በአገሪቱ የተንሰራፋው ሰፊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግር በደርግ ጊዜ ለተጀመረው የፖለቲካ ስደት ተጨማሪ ነዳጅ ሆኖ በአሁኑ ጊዜ ምናልባት የተቀባይ አገሮች □ጸ□ር □□□በቀ □ሄ□□ □ቢ□ □□□ ይቀንሰው ካልሆነ በቀር ስደት ለኢትዮጵያውያን ሊያቆሙት የማይቻል ጉርፍ ሆኖአል:: ይህ እውነት ከሆነ ዘንዳ በአጠቃላይ ስደትንና በተለይ ኢትዮጵያውያንን በሚመለከት የሚደረግ ውይይት ትርፋማ ሊሆን የሚችለው ውይይቱን በሁለት መልክ ማስኬድ ስንችል ይመስለኛል:: □ጨ□ም፤

1. በአጠቃላይ አገርን ዓሎ መሰደድ በአገራችን ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት ላይ የሚያመጣውን ተ□ጽኖ በሰከነ መንፈስና በዝርዝር መመልከትና በተለይ □ፉ ጉዳት ያመጣሉ በሚባሉት ላይ በሰፊ አገራዊ ውይይት ላ□ □ተመሠረተ መፍትሄ መ□ለፅ፤
2. በአንድ ምክንያትም ሆነ በሌላ በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ለአገራቸው ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ እድገት ሊያደርጉ የሚችሉትን አስተዋፅኦ በጥሞና በመመልከት ባላቸው አቅምና ፍላጐት ላይ በመመስረት ከፍተኛውን አስተዋፅኦ ሊያደርጉ የሚችሉበትን መንገድ ማስላትና ይህንንም ማመቻቸት፤

ምንም እንኳን በእኔ እምነት ከላይ በተ.ቁ. 1 ላይ የተነሳውን ጥያቄ በሚመለከት ያለኝ አስተያየት እያደር አሉታዊ እየሆነ የሄደ ቢሆንምና በተለይም ስደት የችግሮች ሁሉ መፍትሄ እየሆነ መታየቱና ይህም እየፈጠረ ያለው ስነ ልቡና ለወደፊት እድገታችን አደገኛ እንቅፋት እየሆነ ይሄዳል □ሚል እምነት ብይዝም፣ በዚህ ላይ ያለኝን አመለካከት ለጊዜው አቅቤ የዛሬው ውይይት በአብዛኛ□ እንዲያተኩር ወደተፈለገበት ከላይ በ2ኛ ተ.ቁ ወደ ተነሳው ጥያቄ ልመለስ::

## በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ለአገር እድገት የሚኖራቸው ሚና

እንግዲህ የአገራችን መሠረታዊ ችግሮችና የሚ□□ኘን አጠቃላይ የመፍትሄ ሃሳቦች በሚመለከትና ስለስደት አጠቃላይ ሁኔታ ያለኝን ግንዛቤ ለመንደርደሪያ ያህል አቀረብኩ በእኔ ግምት ለዚህ ለዛሬ □□□ታችን ዋነኛ ወደሆነውና ወደ መሬ ረሻ□ □□ሁ□ □□ል ልፅባ:: አሁን አገራችን ላለችበት ሁኔታና ከላይ በእኔ ግምት ለችግሮቿ መንስኤ ባልኳቸው የአስተሳሰብ፣ የአስተዳደርና የካፒታል ችግሮች ላይ በትንሹም ቢሆን ስምምነት ካለን ቀሪው ጥያቄ ታዲያ ይህንን ችግር ለመቅረፍ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሚና ምንድን ይሆናል? የሚለው ይሆናል:: በእኔ እምነት ይህን ጉዳይ በሚመለከት የሚደረጉ ውይይቶች ብዙ ጊዜ የሚስቱት ነገር ያለ ይመስለኛል:: ይኸውም በውጭ የሚኖረውን ኢትዮጵያዊ በሙሉ በአንድ ጐተራ ውስጥ በመክተት ለሁሉም አንድ አይነት ሚና ማዘጋጀት ነው:: እንደ እኔ ለረጅም ጊዜ ውጭ አገር ለኖረና የውጭውንና የኢትዮጵያውያን ኑሮ ለተከ□ተለ እንዲህ አይነት አመለካከት ስህተትነቱ ብቻ ሳይሆን በውጭ ከሚኖሩ ኢትዮጵያውያን አገሪቱ ልታገኝ የምትችለውን ሰፊ ጥቅም እንዳታገኝ ያደርጋታል የሚል እምነት አለኝ:: ስለዚህም ለዚህ ውይይት እንዲረዳ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን ለኢትዮጵያ ሊሰጡ ከሚችሉት ጥቅምና ለአገሪቱ እድገት ሊኖራቸው ከሚችለው ሚና አንፃር ብቻ መለያየቱ አስፈላጊ ነ□ ብጽ አምናለሁ:: ወደዚህ ምደባ ከማምራቴ በፊት ግን በአጠቃላይ

በመርህ ደረጃ ሊ□ ሰቡ □ሚ□ቡ ዋና ዋና ነጥቦችን አስቀምጬ ልለፍ፤

(1) በ□·□ □ሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ለአገር እድገት □ሚኖራቸውን ሚና መቀበልና ይህንንም መጠቀም በምንም አይነት ስደትን ማበረታታት እንዳልሆነ ግልፅ ሊሆን ይገባዋል። በተለይ በአሁኑ ጊዜ የስደቱ ቅጥ ማጣት በተለይ የአገሪቱን የተማረ የሰው □□ል በእጅጉ እያመነመነው መሄድ፣ ይህም የአገራችንን የወደፊት እድገት ፍፁም እየተፈታተነው እንደሆነና፣ ከዚያም በላይ ግን ለመሰደድ ያለው ፍላጐት በአገር ውስጥ በሚኖረውም ነዋሪ ዘንድ እየፈጠረ ያለው የግዴለሽነትና የጊዜያዊነት ባህሪ (በትምህርት፣ በሥራ፣ በማህበራዊ ኑሮ... ወዘተ) እጅግ አደገኛና የእድገት ፀር መሆኑ ሁላችንንም ሊያሳስብ የሚገባ መሆኑ፤

(2) አገራችን ካለባት መጠን የለሽ ችግር አንፃር በውጭ ከሚኖሩ ሁሉም አይነት ኢትዮጵያውያን እንደ ኢኮኖሚ አቅማቸው፣ እንደ እውቀታቸውና ችሎታቸው ሊያበረክቱ የሚችሉትን ማንኛ ውንም ቀና አስተዋፅኦ መጠቀም እንደሚገባና ለዚህም መጣር እንደሚያስፈልግ፤

(3) ይህም ሲሆን ግን በምንም መልኩ አካሄዳቸው ከላይ የኢትዮጵያ ችግሮች ብዬ የዘረዘርኳቸውን የሚያባብሱ ሆነው ከተገኙ ቢያንስ እነኝህ በያዙት መንገድ እንዳይበረታቱ መከላከል ይገባል። በውጭ የሚኖር ወይም የኖረ ሁሉ "ዓሩ" ነው ወይንም "አዎንታዊ ሚና ይጫወታል" የሚል ጭፍን የዋህነት ሊኖር አይገባም በመጨረሻም፤

(4) ልክ የውጭ አገር ኢንቬስተሮች ለመሳብ በሚደረገው ጥረት "ትርፋማነት" ዋና መሳቢ.ጸ□· እንደሆነ ሁሉ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ለአገር እድገት እንዲያበረክቱ ዋና መገፋፊያው የአገር ፍቅርና ከአገር ጋር ያለ ትስስር ነው። ስለሆነም በመንግሥት በኩል የአገር ፍቅርን እያዳከሙና □ጸኮሰሱ በ□·□ ካለ□· ኢትዮጵያዊ ይህን ጥቅም መጠበቅ ተላላነት ነው። ስለዚህም በአገር ውስጥ ያለው መንግሥት ኢትዮጵያዊ ብሄረተኛነትን ማሳየት □□ባ□ል።

በጥቅሉ በውጭ የሚኖረውን ኢትዮጵያዊ በአገር እድገት ለማሳተፍ የሚያስፈልጉ ጉዳዩችን በሚመለከት ይህን ያህል ካልኩ፤ ይህን ጥቅም ለማግኘት □ሚጸስ□ል□ □ር□ር □□ዮች ውስጥ ልግባ። በመጀመሪያ ከላ□ እንዳልኩት አገሪቱ የምትፈልገው □ሩ□ ከላይ ያነሳኋቸውን ሶስት ችግሮቻችንን የሚቀርፉ ሊሆኑ □□ባል። እያንዳንዱ በውጭ የሚኖር ኢትዮጵያዊ ደግሞ በነኝህ በሶስቱም ጉዳዮች ላይ ችሎ□ ወይም ብቃት አለው ማለት አይቻልም። ስለዚህም የመጀመሪያው ተግባር መሆን ያለበት በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን በሚመለከት ለውይይት የሚረዳ ምደባ (category) መ□□ር ጸስ□ልፉል። በእኔ እምነት ለውይይታችን እንዲረዳ በውጭ የሚኖረውን ኢትዮጵያዊ ስድስት ጥቅል ም□ባ- ች ማካተት ይቻላል።

ሀ) በተለያየ ምክንያት ካለ□ላ□ቱ (ከኢኮኖሚ ችግሮች ውጪ) ከአገር □□□፤ ቢችልና ሁኔ□□· ቢመቻችለት አገሩ መመለስና ለአገሩ እድገት አስተዋፅኦ ማድረግ □ሚ□ልፅ ግን "ምን ይገቼ ልግባ" የሚለው በጣም የሚያስጨንቅ።

ለ) በተለያየ ምክንያት አገሩ መመለስ የማይችል □□ም የማይፈልግ ግን ውጪ ብዙ ከመቆየት ብዛት ሰ□ ጸለ እውቀት ጸ□በረ (በተለጸ□ ሙጸ)፣ በተጨማሪም የአገሩ ውድቀት የሚያበግነውና ባለው ሙያ (ኑሮው በፈቀደው መጠን) አገሩን ለመርዳት በጣም የሚፈልግ፣ ሆኖም ግሊጋሎቱን በኢትዮጵያ ካለው መንግሥት ጋር በጥብቅ የሚያያይዝ (አገርን መርዳት መንግሥትን መርዳት ነው ብሎ □ሚጸስብ)፤

ሐ) ከላይ በ (ለ) እንደተጠቀሰው ሆኖ ግን የመንግሥት ማንነት ብዙ የማያሳስበውና በሙያው ብቻ መርዳት የሚፈልግ ግን በምን መልክ መርዳት እንደሚችል ያላወቀ ወይንም ሁኔታው ያልተመቻቸለት፤

መ) በውጭ አገር ንብረት ያፈሩ፣ ካላቸው ንብረት በመጠኑም ቢሆን የተወሰነውን በአገራቸው ኢንቬስት ማድረግ የሚፈልጉ ሆኖም (መ-1) ይህን ማድረግ መንግሥትን ማጠናከር የሚመስላቸው ወይም (መ-2) ስለ መንግሥት (ፖለቲካ) ብ□ም ግድ የሌላቸውና ግን አገር ውስጥ ስላለው የቢሮክራሲ ሁኔ□ ከሚሰሙት ብቻ በመፍራት ወደ አገር ኢንቬስት ማድረግን የሚሸሹ፤

ሠ) ኢትዮጵያን ለኑሮ □ማ□መጇት፣ ለችግሯም ብዙ የማያስቡ ግን ለትዝ□□ የሚፈልጓት፣ ስለሆነም በተቻለ መጠን ባገኙት ጊዜና ኑሮአቸው በሚፈቅደው መጠን እየተመላለሱ ሊያዩት የሚፈልጉ፣ በተለይም በችግራቸው ጊዜ (ለሀዘን) □□ንም ለደስ□ (ለሠርፅ) አ□ራቸውን (ዘመዶቻቸውን) የሚፈልጉ። ቢችሉ የጡረ□ እድሜያቸው ሲደርስ አገራቸው □በተ□· ማረ□ □ሚ□ል□ □ህም ግን በሁለት ሊከፈል ይችላል አንድም ለጉራ የሚፈልጓት ሌላም □ም ብለው ለትዝ□□:-

ረ) ከወጡ ጀምሮ ሕይወታቸውን ለኢትዮጵያ ፖለቲካ □ስ□·፣ የኢትዮጵያን የአስተዳደር ሥርዓት ዓሩ ነው ብለው በሚያስቡት መል□ ለመቀ□ር □ሚሹ (ለ□ህም በውጭ ሆነው የሚታገሉ) ከነኝህም ግን፤

1) ለራሳቸው ምንም የፖለቲካ ሥልጣን ፍላጎት የሌላቸው ግን የአ□ሪቱ ዋነኛ ችግር የአስተዳደር ሥርዓት መጥፎነት ነው ብለው የሚያስቡ ስለዚህም ይህን ለማስተካከል የራሳቸውን

አስተዋፅኦ ማድረግ እንዳለባቸው የሚያምኑ:-

2) አገሪቱ ያለ እነሱ መፍትሄ እንደማይኖራት እርግጠኛ የሆኑና የእነርሱ ስልጣን አካባቢ መኖር ምንም ምርጫ የሌለው ብቸኛ መፍትሄ ነው ብለው የሚያምኑ:: ለዚህም ለጊዜው አገሪቱን ጎዳም አልጎዳም ወደ ስልጣን ለሚያደርጉት እንቅስቃሴ እንቅፋት ነው ብለው የሚያስቡትን ሁሉ ለማስወገድ □ሚ□ □ሉ::

ይህን አመዳደብ ሙሉ በመሉም ባይሆን (ከዚህም የዘረዘረ አመዳደብ ማውጣት ይቻላል) በመጠኑ ያስኬዳል ብለን ከተቀበልን ከዚህ □ሚቀዓለ□ እንግዲህ ይህን ኃይል ለአገር እድገት እንዴት መጠቀም እንችላለን የሚለው ነው:: ከላይ በ□ር□ር እንደተጠቀሰው አገሪቱ ልትከተለው የሚገባት እስትራቴጂ እነኝህ የተለያዩ ዜጎች ያላቸውን አቅምና ችሎታ የመዘነና ለእያንዳንዱ ክፍል የተለያዮ አካሄዶች የቀየሰ ሊሆን ይገባል:: በመነሻ የአገሪቱ ችግሮች ያልኳቸውን ሶስት መሰረታዊ ነጥቦች በውጭ የሚኖረውን ኢትዮጵያዊ አይነት ከዘረዘርኩበት ም□ባ (category) ፋር ማ□መድ ዓሩ አቅጣጫ አመላካች □መስለኛል::

በጣም ከሚቀለው ል□ምር:: አብ□ኛ ው በውጭ የሚኖር ኢት□□ጸዊ በነኚህ ሶስት የኢትዮጵያ ችግሮች ዙሪያ ብዙ አስተዋፅኦ ሊያደርግ ይችላል ብዬ ስለማምን አስተዋፅኦቸው አሉታዊ ይሆናል ከምለው ልጀምር:: እነኚህ ከላይ ከመደብኳቸው ውስጥ በተለይ ሁለቱን ይመለከታል እነኚህም::

1) ኢትዮጵያን ለጉራ ብቻ የሚፈለጋትና ይህንንም ለማድረግ በተለይ በአገሪቱ ያለውን "የአስተሳሰብ" ችግር ከመቅረፍ ይልቅ ሊያባብሱ የሚችሉ □ይሎች (ይህንን የሚያደርጉት ግን ሆን ብለው ለመጉዳት ላይሆን ይችላል)፤

2) የአገሪቱ የአስተዳደር ሥርዓት ጸለእነሱ ሥልጣን ላይ መውጣት መፍትሄ እንደሌላው የሚያምኑ ለዚህም የአገሪቱን □ላቂ ዓቅም □ዳም አልጎዳም፣ □□ ሥልጣን ለመውጣት ለሚያደርጉት እንቅስቃሴ እንቅፋት ነው ብለው የሚያስቡትን ሁሉ ለማስወገድ የሚታገሉ፤ ለዚህም ውሸትን፣ ቅጥፈትን፣ አሉባልታን፣ ሽብር መንዛትን፣ ስም ማጥፋትን የትግል ስልት አድርገው የሚጠቀሙ::

እነኝህ ሁለት አይነት ኢትዮጵያውያን በማወቅም ይሁን ባለማወቅ አገሪቱ ውስጥ ላለው ችግር መፍትሄ ከማስገኘት ይልቅ ችግሩን በማባባስ የሚጫወቱት ሚና የላቀ ነው:: ከመጀመሪያው አይነት ኢትዮጵያውያን አንድ ምሳሌ ለአብነት ልጥቀስ፣ ሌሎች ብዙ ምሳሌዎች ማሳየት ይቻላል? ሠርግ::

በኢትዮጵያችን ያለ አንድ መሰረታዊ የአስተሳሰብ ችግር አቅምን አውቆ አለመኖር፣ በተለይም በጣም ጊዜያዊ ለሆኑ ባህላዊ ኩነቶች (ለደስታ፣ ለሀዘን፣ ወዘተ) ያለንን ጥሪት አሟጦ መጠ ቀምና ይህ ሁኔታ ሲያልፍ እራስንና ቤተሰብን አጉል የሆነ የኢኮኖሚ ችግር ውስጥ መክተት ነው:: ለሠርግ ተብሎ ያለንን ንብረት ሸጦ አገር ምድሩን መጋበዝ፣ ተዝካር አወጣለሁ ብሎ የማረሻ በሬውን ማረድና ለዘላለም ከድህነት ጋር መቆራኘት... ወዘተ በጣም ሥር የሰደደ መጥፎ ባህል፣ ለእድገት የሚያስፈልገንን ካፒታል በከንቱ ማባከን መሆኑን በአገር ውስጥ እንኳን ያሉ ሽማግሌዎች ህብረተሰቡን በየጊዜው የሚገስፁበትና በአንዳንድ አካባቢዎችም (ለምሳሌ በገጠሩ የጉራጌ ክፍል) ማህበረሰቡ ተሰብስቦ ውሳኔ ያሳለፈባቸው ጉዳዮች ናቸው:: እንግዲህ ይህ አላዋቂ የሚባል ህብረተሰብ እንኳን ፍሬ ከርስኪነቱን አምኖ ለመተው የሚታገልባቸውን እነኝህን ኋላ ቀር ባህሎች አወቀ፣ መጠቀ ተብሎ የሚባልለት፣ እንደነኚህ አይነት ወጪዎች (በተለይ ከመጠን ሲያልፍ) ጭራሽ እንደ ጅልነት በሚቆጠሩበት አገሮች እየኖሩ ለጉራ ሲባል ብቻ እራሳቸው ከሚኖሩበት አገር አልፈው ኢትዮጵያ ድረስ መጥተው የኔ ወይስ ያንቺ ድግስ ይበልጣል ብሎ ፉክክር ምን የሚሉት አማርኛ ነው? በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እንደሠርግ አይነት የተለየ የደስታ ጊዜአቸውን በአገራችው ለምን መጥተው አሳለፉ አይደለም፤ ነገር ግን ስንት ደክመው ያፈሩትን ትንሽ ሀብት በፍፁም በህይወታቸው አይተዋቸው የማያውቋቸውን በሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን አግበስብሰው ማበላትና፣ በዚህም መኩራስ በፍፁም ቅጥ ያጣ ግብዝነት ነው:: አንዳንድ በውጭ በሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን በእንዲህ አይነት ግብዝነት ለእንዴት አይነት የኢኮኖሚ ችግር እንደሚዳረጉ ይታወቃል:: ሌላው ቢቀር ይህ ወደፊት ለሚወልዷቸው ልጆች አለማሰብ ነው:: ጉራው ከመጡበት አገር ላሉ ወዳጆቻቸው ከሆነ እዚያው ባሉበት ቢያደርጉት ይሻላል:: ለአገራችን ችግር "የአስተሳሰብ ለውጥ" □ፀፅ ያስፈልጋል በምንልበት በአሁን ጊዜ በውጭ ቆይታቸው ይህንን ግብዝነት ይዘውልን የሚመጡት ግን አገሪቱን እየረዱ ሳይሆን እንዲያውም እየጎዱ መሆኑን ሊያውቁት ይገባል::

በሁለተኛ ደረጃ ያስቀመጥቁት ግን ከዚህም የከፋ ችግር የሚያስከትሉ ናቸው:: ችግሩ ደግሞ መጠነ ሰፊ ነው:: የመጀመሪያው ስህተት በብዙ ሺህ ማይሎች ከአገር ርቆ በአገር ለሚመጣ ለውጥ ዋነኛው ወኪል እኔ ነኝ ብሎ ማሰብና ከልብ ማመኑ ቢያንስ እራስን አንቱ

የማለት ለከት የሌለው የበላይነት ስሜት ሲበዛም በስነ ልቡና ሐኪም ሊታይ የሚገባው ሁነኛ የአዕምሮ መዛባት ይመስለኛል:: ሁለተኛ እንደዚህ በርቀት ሆኖ ለውጥ ለማምጣት የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች በተቻለ መጠን በድርጊት የሚያሳያቸው ብዙ ተምሳሌቶች ሊኖሩ ይገባል:: በተለይም እንደነኝህ አይነት ኃይሎች በአብዛኛው የሚገኙት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በሰፈነባቸው የምዕራብ አገሮች እንደመሆኑ ከዚያ የፖለቲካ ልምድ በመቅሰም ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚጠናከርበትን መንገድ፣ መቻቻልን፣ መደማመጥን የዴሞክራሲያዊ ፖለቲካ አካሄዶችን በማሳየት በአገር ውስጥ ያለውን ብዙ ማስተማር ሲገባ ይብሱኑ ፍፁም በውሸትና በማደናገር ላይ በተመሰረተ፣ እጅግ ጊዜው ባለፈበት (በኢትዮጵያ እንኳን) የበሬ ወለደ ፖለቲካ በውጭ የሚኖረውን አልፎ በአገር ውስጥ ያለውን ህዝብ ነገ ውሸትነቱ በሚታወቅ ከንቱ ፕሮጠጋንዳ ለማደራጀትና በዚያ አቋራጭ ሥልጣን ላይ ለመንጠላጠል መባዘን ከአፍራሽነቱም በላይ በፍፁም በጤንነት የሚታይ አይደለም:: በእኔ እምነት ከአሁን በኋላ (እንደ ከዚህ በፊቱ) በአገራችን ለውጥ የሚመጣ ከሆነ (ለውጥ መምጣት እንደሚያስፈልግ ከላይ ገልጨዋለሁ) በአገር ውስጥ ባሉ ኃይሎችና በማህበረሰቡ ሰፊ እንቅስቃሴ ብቻ ነው የሚሆነው:: ከዚያም በላይ፣ ለአገራችን ጤናማ ኑሮ የምንመኝ ከሆነ ዘንዳ ሊመጣ የሚገባው ለውጥ ሰላማዊና ብዙው የህብረተሰብ ክፍል መብቴን አስከብራለሁ ብሎ የሚነሳበት አይነት እንቅስቃሴ ነው:: ስለዚህ እንደነኝህ አይነት ኃይሎች ምንም እንኳን ቁጥራቸው በጣም አናሳ ቢሆን በእምነታቸው አክራሪነት ምክንያት ሊያደርሱ የሚችሉትን አደጋ ከወዲሁ በመገንዘብ፣ ሲሆን ይበልጥ አዎንታዊ የሆነ የፖለቲካ አካሄድ የሚይዙበትን ካልሆነም ግን ከዚህ አፍራሽ ድርጊታቸው እንዲታቀቡ በአገር ውስጥም ባሉ የፖለቲካ ተቃዋሚዎችም ሆነ በውጭ በሚኖሩ አብዛኛ□ ኢትዮጵያዊያን በማያ□ላዳ መንገድ ሊገለፅላቸው ይገባል:: "የጠላቴ ጠላት ወዳጄ ነው" □ለቲካ ኢትዮጵያ አሁን ላለችበት "የአስተዳደር ችግር" በምንም መልኩ መፍትሄ አይሆንምና! ሙሉ ጊዜዬን አገሬቱ የፖለቲካ ለውጥ ለማምጣት ማዋል እፈልጋለሁ ለሚል ግን ይህ መብቱ ብቻ ሳይሆን በዚህም አገሩን መጥቀም ይችላልና ሊበረታታ ይገባዋል:: ይህንን ማድረግ የሚቻለው ግን በአገር ውስጥ ብቻ ነውና አገራችሁ ገብታችሁ ይህንን አድርጉ እላለሁ:: አሉታዊ ሚና □□ □ታሉ ባልኳቸው ላይ በጥቂቱ ይህን ካልኩ ይበልጥ አ- ን□ዊ ሚና ሊጫወቱ በሚችሉት በአብዛኛው ኢትዮጵያውያን ላይ በማተኮር ንግግሬን ላብቃ::

በመጀመሪያ፣ በተለያየ ምክንያት ከአገሩ ውጪ መኖር የማይፈልገውና ቢመቸው አገሩ ተመልሶ መኖርና መሥራት የሚፈልገውን በሙሉ የሚመለስበትን መንገድ ማመቻቸት ያስፈልጋል:: በርግጥ አገሬቱ አሁን ባለችበት ሁኔታ ለእንደዚህ አይነት ሰዎች ሁሉ የተዘጋጀ ሥራ ላይኖራት ይችላል:: ሆኖም በአብዛኛ □ እንዲህ አይነት ሰዎች ተቀዓ ረ□ ለመሥራት ሳይሆን መመለስ □ሚ□ልጉት ወይንም በሙያቸው አሊያም እራሳቸውን ለማስተዳደር የሚያስችል አነስተኛ ሥራ ይዘው ነው አገራቸው መግባት የሚፈልጉት:: በተለይ በአውሮፖ አሁን ባለው "□ረ ስ□ተኛ" ስሜት ምክንያት አንዳንድ የአውሮፖ አገሮች እንዲህ አይነት ሰዎች ወደ አገራቸው ሲመለሱ ለመቋቋሚያ የሚሆን አነስተኛ ካ□ታል ለመስጠትም ፈቃደኞች ሆነዋል:: እነኝህ ኢትዮጵያውያን በተለይ በኖሩበት አገር ያለውን የሥራ ስሜት (work ethic) ከልባቸው ከያዙት ባለቻቸው ትንሽም ጥሪት ቢሆን ኢትዮ□ጸ መዓተ□ ሊሰሩ፣ ንብረት ሊያፈሩ ምናልባትም ለሌሎች ዜጐች የሥራ □□ል ሊ□ዓሩ ይችላሉ:: በተለይ ጠንካራ የሥራ ባህል ያላቸው ከሆኑና ምንም ይሁን ምን ያላቸውን ሙያ ከምር ከወሰዱት በአገራችን ያለውን የሥራ መንፈስ በመቀየር በኩል ሁነኛ አስተዋፅኦ የሚኖራቸው ይመስለኛል:: ይህንንም ለማገዝ በየአገሩ ጸሉ የኢትዮጵያ ኮሙኒቲ ማህበራት ሁነኛ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ::

በሁለተኛ □ረጽ ጸለ□ ለረፀም □□ በውጭ በመኖር ብዙ እውቀትና የሥራ ልምድ ያካበተውን ይመለከ□ል:: □ህ ኃ□ል በ□ም ብዙ ሚና ሊጫወት የሚችል ግን □ስካሁን በቅጡ ያልተጠቀምንበት ኃይል ነው:: በመጀመሪያ ከዚህ ኃይል ውስጥ ብዙው ለማለት ይቻላል "ኢትዮጵያን በምንም መልኩ መርዳት መንግሥትን መርዳት ነው" በሚል አገርንና መንግሥትን በማይለይ የተዛባ አመለካከት የተወናበደውን ወደ ትክክለኛ አስተሳሰብ መመለስ □□ባል:: ይህም በጣም ከባድ ሊሆን አይገባም:: አንድም ይህ አስተሳሰብ ሀሰት የሚሆንባቸው ብዙ ምሳሌዎች ማሳየት ይቻላል:: ለምሳሌ ብዙ ሙያተኞች ከመንግሥት ጋር ብቻ ሳይሆን ከመንግሥት ውጪ ያሉ የየሙያ ማህበራት ጋር የእውቀት ልውውጥ ሊያደርጉ ይችላሉ:: ይህን በማድረጋቸውም መንግሥትን አለማጠናከራቸው ብቻ ሳይሆን መንግሥትን የሚቋቋሙ ጠንካራ የሙያ ማህበራት እንዲኖሩና እንዲጉለብቱ ሊረዱ ይችላሉ:: ይህም ማለት ኢትዮጵያ ከመንግሥት ጋር ያልተነካኩ ብ□ የሲቪል ማህበረሰብ አካላት ያሉባት አገር እንደመሆኗ መንግሥትን መሸሽ ለሚፈልጉ ባለሙያዎች ብዙ እድሎች አሉ:: በሌላ በኩል ግን በጊዜያዊነት መንግሥትን ይረዳልና ይህ ከሚሆን ህዝቡ ይጉዳ የሚል

አስተሳሰብ (ለምሳሌ፤ በረሀብ □ተ□ዱትን ከመርዳት ዝም ብሎ መቀመጥ) በጣም ከጠባብ ስሜት የመነጨ በህዝብ ህይወት ቁማር የሚጫወት አስተሳሰብ ብቻ ነው የሚሆነው::

ይህንን የመጀመሪያውን መሰና□ል ካለፍን በኋላ ግን በውጭ የሚኖሩ □ተማሩና ባለሙያ ኢትዮጵያውያን ለአገራችን እድገት በሁሉም መስኩ ሊያደርጉ የሚችሉት አስተዋፅኦ በ□□ም በቀላሉ □ሚ□□ አይደለም:: □ህ እውቀት ደግሞ እንደ ኢትዮጵያ ላሉ አገሮች ለማ□ፅ እጅግ ከሚያስፈልጓቸው ነገሮች ዋናዎቹ ናቸው:: ብዙ ኢትዮጵያውያን በጤና፣ በትምህርት፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ በሳይንስ ወዘተ... መስክ ስመጥር በሆኑ በውጭ አገር ተቋሞች ይሠራሉ:: ይህን እውቀትና የሥራ ልምድ አገራቸው ለሚ□ኙ መሰል ባለሙጸዎች ቢያስተላልፉት አገሪቱ እንዲህ በቀላል የማይሰላ ጥቅም ነው □ም□ □ኘ□:: በእነኝህ ሙያተኞች ለመ□ቀም እነኝህ ሰዎች ወደ አገራቸው መመለስ የለባቸውም፣ ባሉበት ቦታ ሆነው ለትውልድ አገራቸው ብዙ ሊሰሩ ይችላሉ:: □ህ እንዲሆን ግን በውጭ በሚኖሩትም፣ አገር ውስጥ ባሉትም ኢትዮጵያውያን ትንሽ ጥረት ያስፈልጋል:: አገር ውስጥ ያሉት ሙያተኞች በውጭ ካሉ ወገኖቻቸ□ ለመ□ቀም እንዲቻል ሁኔታዎችን ማመቻቸት ጸስ□ልፉል:: በተለ□ም እነኝህ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሙያተኞች ሁልጊዜ ስለ ኢትዮጵያ እንዲያስቡና በዚህም ዙሪያ ጥናት እንዲያዘጋጁ መወትወት ያስፈልጋል:: በአገር ውስጥ በአመት አንድ ጊዜ የሚደረጉ የሙያ ማህበራት አመታዊ ኮንፍረንሶች ለዚህ አይነተኛ መሳሪያ ሊሆኑ ይችላሉ:: በመንግሥትም ሆነ በግል የትምህርት ተቋማት በተወሰነ ጊዜ □ረፀም □□ እረፍታቸውን ሲወስዱ አገራቸው መጥተው ለጥቂት ወራት የሚሰሩበትን መንገድ ማመቻቸት ሌላው መንገድ ነው:: አገሪቱ ውስጥ ባሉት አገራዊ የንግድ ተቋማት ወይንም አገራዊ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ጋር ለጥቂት ሳምንታትም ቢሆን እያመጡ ልምዳቸውን ቢያካፍሉ ወይንም ዝም ብለው አብረው ቢሰሩ እነሱም በአገሪቱ ስላለው የንግድ ችግር ይማራሉ አገር ውስጥ ያሉ ተቋማትም በሌላው አገር ያለውን አሰራር ይማሩበታል:: ሌላ ቀርቶ አገራቸውን በጣም በወጣትነታቸው የለቀቁ ወይንም □□ጸ □ተ□ለዐ ወላጆቻቸው ኢትዮጵያውያን የሆኑ ወጣቶች ትምህርታቸውን ገና የጨረሱና ለመጨረስ የተዳረሱ ተማሪዎች የሁለት ወር የክረምት እረፍት ግዚያቸውን አገራቸው መጥተው በአገር ካሉ ተቋማት ጋር በልምም□ (internship) መል□ ቢሰሩ የአገራቸውን ችግሮች በቅርቡ እንዲያዮ ከዚያም ከአገሪቱ ጋር ያላቸውን ትስስር ሊያጠናክሩ ይችላሉ:: በተለይ በህክምና ዘርፍ □ተሰማሩ ኢትዮጵያውያን (አብዛኞ- ቹ ማለት ይቻላል በአገራቸው የነፃ ትምህርት ተምረው የሄዱ) ለትውልድና ላስተማራቸው አገር አገልግሎት የመስጠት የሞራል ኃላፊነትም ጭምር ሊሰማቸው ይገባል:: ብዙዎቹም ይህ ስሜት የሚሰማቸውና በተቻላቸው አገራቸውን የሚያገለግሉበት መንገድ ቢፈጠር የሚፈልጉ □መስለኛል:: ሁኔታውን ማመቻቸት ከተቻለም ጠቀሜ□□ መሠረታዊ ነው የሚሆነው:: ለምሳሌ ጸህል በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የህክምና ባለሙያዎች በግልም ሆነ በስብስብ (በፅሩኘ) በአመት አንድ ጊዜ ለተወሰነ ጊዜ (ለሳምንታት) ኢትዮጵያ እየመጡ አገልግሎት ሰጥተው ሊመለሱ ይችላሉ:: ከተባበሩና ከ□በዙ ይህንን ግልጋሎት ሊሰጡ የሚችሉባቸው መሳሪያዎች □□ጸ□ በ□ር□□ ማፅኘት የሚችሉ ይመስለኛል:: በአገር □ስዓ □ሚ□ኙ □ሙጸ ጓደኞቻቸውና መንግሥት ሲመጡ □ሚሰሩበትን ቦ□፣ ካስ□ለ□ም መኖሪያ በቋሚነት ሊያዘጋጁላቸው የሚችሉ ይመስለኛል:: እነኝህ ለአብነት የጠቀስኳቸው የትብብር መስኮች በጣም ጥቂቶቹ ናቸው:: ቅን ልቦናው ካለና ለአገራችን የጋራና ውስብስብ ችግሮች በረጅሙ ማየት ከቻልን ያለ ብዙ ወጪ ለአገሪቱ ዘላቂ ጥቅም የሚያስገኙ ብ□፣ እጅግ ብዙ ነገሮች ማድረግ ይቻላል:: በዚህ አጋጣሚ የኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር አመ□ዊ ኮንፍረንሱን ከአምና ጀምሮ አለማቀፍዊ ያደረገውና በተለይም በ□ረምቱ መፅቢጸ ላ□ ጸ□ረ□□ ሆን ብሎ እንዲህ አይነቱን □እውቀት ልውውጥ ለማበረታታት ስለሆነ የአገሪቱን እድገት በሚመለከት አስተዋፅኦ ያደርጋሉ የሚባሉ ማናቸውም የምርምር ውጤቶች (በተለይ በኢኮኖሚክስና በማህበራዊ ሳይንስ ዘርፍ) በውጭ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እንዲቀርቡ በ□ም □በረ□□ል::

በሶስተኛ ደረጃ ያለው ምንም አከራካሪ ያልሆነው ነው:: ይኸውም በውጭ አገር በመኖር ንብረት ያፈራው ኢትዮጵያዊ ነው:: ይህ እስከአሁን ካለው መረጃ በቁጥር በጣም አናሳ የሆነ ግን ሊኖረው የሚችለው አስተዋፅኦ አይነተኛ ነው:: □ዚህ ላ□ ሊ□□ □ሚ□ብ□ እነኝህ ባለሀብቶች ከሌላው ባለሀብት ፉር ሲ□□ □ፀፅ □ላቀ ካ□□ል ስላላቸው አይደለም (ምናልባት በጣም ከጥቂቶች በስተቀር):: ነገር ግን አገሪቱ ካለባት የውጭ ምንዛሪ እጥረት አንፃር ሲታይ፣ እነኝህ ሰዎች ካላቸው የውጭ ትስስርና ግንኙነት (contacts)፣ ስለ አለም አቀፍ የንግድ ማእቀፍ የሚኖራቸው እውቀትና በዚህም ማእቀ□ □ስዓ ተወዳድሮ ለማሸነፍ ስለሚያስፈልጉ የንግድ አሰራሮች ያላቸው ተሞ□ሮ ለአገሪቱ ትልቅ እሴት አለው:: የኢትዮጵያ መንግሥት ለእድገታችን ወሳኝ የውጭ ኢንቬስትመንት ነው በማለት የውጭ ኢንቬስትመንት አገር ውስጥ ለማስገባት ሲዳክር ይኸው አሥር አመታት አለፉ:: ምንም ይኸ ነው የሚባል የውጭ ኢንቬስትመንት አልመጣም::

በተደጋጋሚ በአገር ውስጥ ውይይቶች ለማቅረብ □ንደሞከርኩት ይህ በፍፁም ሊገርመን አይገባም:: ከሌሎች አገሮች እንማር ካልን (ቬየትናም፣ ቻይና፣ ህንድ ወዘተ...) ትርፍ ፍለጋ የሚመጣ የውጭ ሀብት በመጀመሪያ በዚያ አገር ይህ ነው □ሚባል □እድገት እንቅስቃሴ መኖሩን ሲያይና ሲያምን ነው ወደዚያ አገር ካፒ□ል □ሚጸ□ሰው:: ይህ ሁኔ□ እንዲፈጠር ግን በመጀመሪያ በአገር ውስጥ የሚኖረው ባለሀብት፣ ከዚያም በውጭ የሚኖሩ የአገሩ ዜጐች ስለአገሪቱ የወደፊት ህይወት ብሩህ ተስፋ ሊኖራቸውና ይህንንም ተስፋቸውን ያላቸውን ንብረት በማሰራት ሊያሳ□ት ይገባል:: እነኚህ ሁለት ኃይሎች ደግሞ ከውጪው ባለሀብት ይልቅ ይህንን ለማድረግ የሚቀድሙት አንድም ስለአገሪቱ የበለጠና የጠለቀ እውቀት ስላላቸው በዚህም ለውጭው ባለሀብት "አብሪ" ሆነው ሊያገለግሉ በመቻላቸው ሌላም ከትርፍም በላይ አገራዊ ስሜት ስለሚኖራቸው ነው:: ስለዚህም ነው ካፒታል ከውጭ እንዲመጣለት የሚፈልግ መንግሥት ከምንም በላይ ይህንን ኃይል ሊንከባከብ የሚገባው::

ይህንን ኃይል ማንቀሳቀስ ግን እንዲህ በቀላሉ "መኪና ከ□□ስ □·□ □ስ□ባለህ" በሚል የሚዘልቁት አይደለም:: ለማግባባት □ሚሞከረው ኪሱን ብቻ ሳይሆን ብሄራዊ ስሜቱን በመኮርኮር እስከሆነ ዘንዳ ያንን ብሄራዊ ስሜቱን ለማነሳሳት የሚያስችሉ ከወሬ ያለፉ ሁነኛ እርምጃዎች በተግባር ሲወሰዱ ብቻ ነው ይህ ሊሆን የሚችለው:: ከዚህ ውስጥ አንዱን (አጠቃላይ ኢትዮጵያዊ ብሄርተኝነትን) ለዚህ ክፍል ብቻ ሳይሆን በጥቅሉ ለምን አስፈላጊ እንደሆነ ከላይ ጠቅሼዋለሁ:: ከዚህም በላይ ግን የንብረት ዋስትና፣ የአገሪቱ ህዝብ (የራሱን ጨምሮ) የሰብአዊ መብቶች መከበር፣ መልካም አስተዳደር መኖር፣ በአብዛኛ□· ህ□ብ ተቀባይነት ያለው ዴሞክራሲያዊ □□ለቲካ ሥር□ት፣ የሚሰራ የፍትህ ሥር□ት ወዘተ... እንዲህ አይነቱን ከአገሪቱ ጋር ጥብቅ የሆነ የስሜትና የማህበራዊ ትስስር ላለው በውጭ ነዋሪ አስፈላጊ ይመስለኛ ል:: እነኚህ ሁኔታዎች ባልተሟሉበት፣ ከዚህ ክፍል ሊገኝ የሚችለው የካፒታልም ሆነ የልምድ አስተዋፅኦ በእጅጉ አናሳ ሲሆን ይ□□ኛል:: □እነኚህ ነገሮች መስተካከል በ□ርፅዓም ዓቅሙ ከዚህም በላይና መጠነ ሰፊ መሆኑን ቀ□ም ብጽ በ□ር□ር □ቅሼ□ለሁ:: በጠባቡ ስናየው እንኳን የነኚህ ሁኔታዎች በቅጡ አለመስተካከል ሊ□ዓሩ የሚችሉትን እንቅፋቶች ለማመላከትና ለማስረገጥም ነው::

በአራተኛው ምደባ ያስቀመጥኩት አንድ ወጥ ያልሆነ በጣም □ተ□ሳሰበ በዓቅሉ "ሰ□□· ስ□ተኛ" ተብሎ ሊቀርብ የሚችል ነው:: ምናልባትም ስገምተው አመልማል አባተ "ምነው ልቤን ስደት ስደት አለው" ብላ የዘፈነችለት ክፍል ነው::

ይህ ክፍል የአገር የኢኮኖሚ ሁኔ□ ጨለማ ሆኖበት የተሻለ ኑሮ ፍለጋ የወጣ፣ ከአዲሱ አገር የእለት ተዕለት ኑሮ ጋር ግብግብ የገጠመ፣ ኑሮውን ለማሸነፍ ሲወጣ ሲወርድ የሚውል ስለዚህም በትውልድ አገሩ ያለውን ሁኔታ በቅርቡ ለመከታተል □□□·ም፣ □ልበቱም □ሌለ□· (እንደው የተለየ ሁኔታ ካልተፈጠረ በቀር ) ግን ከሥራ ወጥቶ ሊዝናና ቢ□ልፅ ጻ□ፉን ልጆች የሚፈልግ፣ ቤቱ ሲገባ ወይንም ከሥራ □□ ቤቱ ሲሄድ በመኪና ውስጥ የአገር ዘፈን (ወይንም ሌሎች ቀልዳ ቀልዶች) የሚሰማ ስለዚህም የውስጥ ስሜቱ በፍፁም ከአገሩ ያልተለየ፣ አቅሙ በፈቀደ መጠን አገሩ እየተመላለሰ ትዝታውን ማደስ የሚፈልግ፣ በህይወት ዘመኑ ካሉት ትልቅ አላማዎች አንዱ (ምናልባትም ዋነኛ□·) አንድ ቀን የኢኮኖሚ ሁኔታውን በደንብ አመቻችቶ ሲሆን ቀደም ብሎ ካልሆነም ቢያንስ ጡረታውን አስከብሮ፣ ትንሽ ገንዘብ ቋጥሮ፣ ዓሩ ቤት በአገሩ ሠርቶ መኖር □ሚ□ልፅ በ□ህ በ□·ረታ ዘመኑም □ም ብሎ መኖር ሳይሆን ስለግል ኢኮኖሚው ብዙ ሳይጨነቅ ለትውልድ አገሩ ትንሽም ብትሆን አስተዋፅኦ ለማድረግ የሚፈልግ ነው::

□ህ ኃ□ል እውነተኛ□· □ምቅ የአገር ኃይል ነው:: ምናልባትም ባልሳሳት ከላይ በሰንጠረዥ አንድ ላይ በውጭ ከሚኖሩ ሰዎች ወደ ኢትዮጵያ የሚላከው ገንዘብ በጣም አብዛኛው ከዚህ ኃይል በአገር ያሉ የተቸገሩ ዘመዶች ለመርዳት የሚላክ ገንዘብ ይመስለኛል:: □ህ □ፅሞ በእኔ ግምት ገና ምንም ያልተነካ እምቅ ሀብት ነው:: ከዚህ እምቅ የሰውና የገንዘብ ኃይል አገሪቱ በሰፊው ልትጠቀም ትችላለች:: ይህን ለማድረግ ግን በመጀመሪያ ይህንን የአገር ስሜትና ት□ታ እንዲቀጥል መደረግ አለበት:: ከዚህም በላይ ግን ይህ ህዝብ የወደፊት ህይወቱን ኢትዮጵያ ለመኖር ያለውን አላማ በሰ□□· ማበረታታት ይገባል:: ይህንን ካመነና ለተግባራዊነቱም ከተንቀሳቀሰ ሌላው ቀርቶ ለራሱ አንድ የመኖሪያ ቤት ቢሰራ በዚህ ምክንያት ወደ አገር የሚገባው □ካ□□ል (የውጭ ምንዛሪ) መጠን በራሱ ብቻ እስከአሁን ወደ አገራችን የሚገባውን ጠቅላላ የውጭ ካፒ□ል ፍሰት በእጅጉ ይልቃል:: እንዲሁ በኤንቬሎኘ ጀርባ በሚደረግ ትንሽ ስሌት ለማሳየት ያክል አሁን በውጭ አገር (በበለፀጉ አገሮችና በአረብ አገሮች) የሚኖረው ኢትዮጵያዊ አምስት መቶ ሺህ ግድም ነው ብንልና (ከዚህ እንደሚልቅ ብዙ ማስረጃዎች አሉ) ከዚህ ውስጥ ግማሹ ብቻ እንኳን በ□·ረ□ □□ው አገሩ ለመመለስና ለመኖር ስለዚህም በአገሩ ቤት መሥራት ይፈልጋል ብንል፣ ይህ በአገሩ ለመሥራት □ሚፈል□ው ቤት በአማካይ 50,000 የአሜሪካን ዶላር ያወጣል ብንልና ይህ ህዝብ በሚቀጥሉት 30 አመታት ውስጥ □□·ረ□ □□ሜ□· ደርሶ (በተለጸ□ □□) □·ረታ ይወጣል ብንል ይህ

ወደ አገሪቱ የሚያስገባው □ክ□□ል ፍሰት በ30 አመት 12.5 ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ወይንም በአመት ወደ 417 ሚሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገደማ ነው:: ይህም አገሪቷ በአሁኑ ጊዜ የምታገኘውን የውጭ ኢንቬስትመንት (የሚድሮክን ጨምሮ) አራት አምስት እጥፍ ይሆናል:: በአገራችን ኢኮኖሚ ላይ የሚያመጣውም ለውጥ ቀላል አይሆንም:: ከሚገኘው ገንዘብ በላይም ግን የዚህ አይነት ስሜት በኢትዮጵያውያን መሰረፁ ሰፊ ፋይዳ ያለው ይመስለኛል:: እንዲህ አይነት ተጨባጭ ንብረት በትውልድ አገራችው ሲኖራቸው በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ከአገራቸው ጋር የሚኖራቸው የፖለቲካ የባህልና የእውቀት ትስስር በዚያው ልክ መሬት የረገጠ ይሆንና በሌላው መስክ የሚኖራቸውን አስተዋፅኦ የበለጠ ያጎላዋል::

በመጨረሻ በአጭሩ ጠቅሼ የማልፈው ስደተኛ ኢትዮጵያዊ የአገሪቱ የአስተዳደር ሥርዓት የሚያሳስበው፣ የዚህ ሁኔታ መስተካከል ለአጠቃላይ የአገሪቱ እድገት ወሳኝ መሆኑን የሚያምን በተለይም አገሪቱ የሰዎች መብት የሚከበርባት፣ ፍትህ የሰፈነባት፣ መንግሥት በህዝቧ ቁጥጥር ሥር የሆነባት አገር እንድትሆን ማየት የሚሹ ቅንና አገር ወዳድ ኢትዮያውያንን ነው:: እነኝህ ሰዎች ማንም በካፒታልም ሆነ በእውቀት ከሚያደርገው አስተዋፅኦ በላይ ለአገራቸው ሊያበረክቱ ይችላሉ:: ከላይ እንደጠቀስኩት የአገራችን አንድ ዋና ችግር የአስተዳደር በተለይም የውስጥ ነፃነት ማጣት ነው:: ይህንን ለመቅረፍ በአገር ውስጥ ለሚደረጉ እንቅስቃሴዎች በውጭ የሚኖሩ ኢትዮያውያን ከፍተኛ የሞራልና የትብብር ድጋፍ ሊሰጡ ይችላሉ:: በአገሪቱ የሰብአዊ መብቶች ሲጣሱ በአለም አቀፍ ደረጃ ድምፃቸውን በማሰማት ያጋልጣሉ፣ የዴሞክራሲያዊ አስተዳደር በሰፊው እንዲመሰረት (የምርጫን ፍትሃዊነት፣ የሚዲያን ነፃነትና ገለልተኝነት ወዘተ...) በሚኖሩባቸው አገሮች ባሉ መንግሥታት በኩል ግፊት ያደርጋሉ፣ በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲጠናከሩ አስፈላጊ ናቸው በሚሏቸውና ከውጭው አገር ልምድ በመነሳት ትምህርታዊ ፅሁፎችን ያዘጋጃሉ ይህንንም በአገር ውስጥ ለሚኖረው ህዝብና የፖለቲካ ድርጅቶች ያሰራጫሉ:: ይህ ሁሉ በጣም ሰፊ ፋይዳ ያለው ሥራ ነው:: ጥቅሙም የአጭር ጊዜ ሳይሆን የረጅም ጊዜ፣ የተወሰኑ የፖለቲካ ድርጅቶችን ከመደገፍና ከመቃወም ይልቅ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሂደቱን ለመርዳትና ይህንን ሂደት ለማደናቀፍ በሚሞክሩ ሁሉም አይነት የፖለቲካ ኃይሎች ላይ ያነጣጠረ በትር መሆኑ ሰፋ ያለ ድጋፍና በአገር ውስጥ ተቀባይነት ያጎናፅፈዋል:: ምክንያቱም ወገናዊነቱ ለፖለቲካ ድርጅቶች ሳይሆን ለአገርና ለዴሞክራሲታዊ ሥርዓት ስለሚሆን:: እንዲህ አይነት ሰፊና የተቀናጀ እንቅስቃሴም በትውልድ አገራቸው ብቻ ሳይሆን በሚኖሩበት አገርም ያሉን የፖለቲካ ኃይሎች ለዚህ ጉዳይ ለማሳተፍ የሚቀላቸው ይመስለኛል::

## ማጠቃለያ

እንግዲህ ከላይ ዘርዘር አድርጌ ለማሳየት እንደሞከርኩት አገራችን ያለችበት ሁኔታ አሳዛኝና ከሁሉም ዜጎች ድጋፍንና ትብብርን የምትሻበት ጊዜ ነው:: የችግሮቹ መፍትሄዎች በጥቅሉ የአስተሳሰብ የአስተዳደርና የካፒታል እንደሆኑ በጥቅሉ ለማሳየት ሞክሬአለሁ:: በዚህ ዙሪያ ከዚህም ዘርዘር ያሉ ብዙ ነገሮች ማለት ይቻላል:: እነኝህ ሀሳቦች ለውይይት መነሻ የቀረቡ እንደመሆናቸው ሌሎች ወገኖች የበለጠ አስበውበትና ተጨንቀውበት ከዚህም የበለጠ ለእውቀታቸን የሚረዳ ዝርዝር ሀሳቦች ይዘው እንደሚቀርቡ ተስፋ አለኝ::
እነኝህን ችግሮቻችንን ለመፍታት በአገር ውስጥ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ትልቁን ሚና እንደሚጫወቱ ምንም ጥርጥር የለኝም:: ሆኖም ግን ለብቻቸው በቀላሉ የሚወጡት ችግር ሳይሆን በውጭ ከሚኖሩ ወገኖቻቸው ጋር በመተባበር ብቻ ነው ሊያደርጉት የሚቻለቸው:: ይህ እንዲሆን ግን በውጭ የሚኖሩ ኢትዮያውያንን በአንድ ስልቻ እንዳለ ድንች አንድ ወጥ አድርጎ ከመውሰድ ይልቅ ትንሽ አፍታቶ ማየት ይጠቅማል በሚል ለዚሁ ጥቅም እንዲውል ብቻ በታሰበ ምደባ ለመመደብ ሞክሬአለሁ:: በነገራችን ላይ ይህ አይነት ምደባ በተቀናጀና ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ በደንብ ቢሰራ (በተለይ ውጪ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን) በጣም ብዙ እውቀት የሚያስጨብጠንና ስለሆነም ሰፊ ፋይዳ ያለው ይመስለኛል:: ከዚህ ምደባም በመነሳት አገሪቱ እንዴትና በምን መልኩ በውጭ ከሚኖሩ ዜጎቿ ልትጠቀም እንደምትችልና እንደሚገባት ለማመላከት ሞክሬአለሁ::

ይህ አቀራረብ በትንሹም ቢሆን በውጭ የሚኖሩ ኢትዮያውያን ይጎነትላል የሚል ተስፋ አለኝ:: ምክንያቱም ይህ ጉንተላ የሚያስነሳው ክርክር፣ ይህ ክርክር የሚገፋፋው ዝርዝር ጥናት፣ ከእነኚህ ጥናቶች በመነሳት የሚደረጉ ሌሎች ውይይቶች ከዚያ በኋላ (አንዳንዴ አገራችን እንዳለው ማለቂያ የሌላው የዘወትር ሰብሰባ እንዳይሆን) የሚወሰዱ የድርጊት እንቅስቃሴዎች ናቸው ለምንወዳት፣ በህሊናችን ሁሌ የምናስባት ግን ከአለሙ ሁሉ ወደ ኋላ እየቀረች ላስቸገረችንና፣ አንዳንዴ ለምታሳፍረን አገራችን ሁለት እርምጃ ወደፊት እንድትራመድ ከከንፈር መምጠጥ ያለፈ አስተዋፅኦ ልናደርግላት የሚያስችለን::

አመሰግናለሁ!